# እንድ አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 312 ሐምሌ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡- ኢዮብ ተፈራ

የቁልፍ ርክክብ ስነስርዓት

## ጠቅላይ ምክር ቤቱ ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋን በፕሬዚዳንትነት መረጠ

### - ተመራጮቹም ሕዝበ ሙስሊሙን ለሰላምና ለልማት በማስተባበር እንደሚሠሩ ገለጹ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የጠቅላላ ጉባዔ እና የሥራ አስፈጻሚ አባላትን ትናንት መርጧል። ጠቅላይ ምክር ቤቱ ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋን በፕሬዚዳንት፣ ሼህ አብዱልከሪም ሼህ በድረዲን እና ሼህ አብዱልዐዚዝ አብዱልወሊን በምክትል ፕሬዚዳንትነት እንዲሁም ሼህ ሀሚድ ሙሳን በዋና ፀሐፊነት መርጧል። ተመራጮቹም ሕዝበ ሙስሊሙን ለሰላምና ለልማት በአንድነት በማስተባበር እንደሚሠሩ ገልጸዋል።

ከቀድሞው የምክር ቤቱ አመራሮች ጋር የቁልፍ ርክክብ በተደረገበት ወቅት አዲሱ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋ፤ የሕዝብ ሙስሊሙን አንድነትን በማጠናከር ሕዝቡ ለሰላምና ለልማት እንዲተባበር እንሠራለን ብለዋል።

ጠቅላይ ምክር ቤቱ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ፒተር አማን

## ሰርጎ ገቦችን ለመከላከል ከአዋሳኝ ዞኖች ጋር በጥምረት እየሠራ መሆኑን የጋምቤላ ክልል አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የክልሉን ሰላም አስተማማኝ ለማድረግ ሰርጎ ገቦችን ለመከላከል ከአዋሳኝ ዞኖች ጋር በጥምረት እየተሠራ መሆኑን የጋምቤላ ክልል አስታወቀ፡፡ በቅርቡ በክልሉ ከተፈጠረው የጸጥታ ችግር ጋር ተያይዞ የጠፋ የሰው ሕይወትና የወደመውን ንብረት በተመለከተ የሚያጣራ ቡድን መቋቋሙም ተጠቁሟል፡፡

የጋምቤላ ክልል ፕሬዚዳንት የማኅበራዊ ጉዳዮች አማካሪ አቶ ፒቴር አማን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ከለውጡ ወዲህ በብዙ አካባቢዎች የተስተዋለው የጸጥታ ችግር በአንጻራዊነት በጋምቤላ ሰላም ሰፍኖ ነበር፡፡ በቅርቡ ግን ባልተገመተ ሁኔታ ሸኔ ወደ ክልሉ ሰርጎ በመግባት በጋምቤላ የሚንቀሳቀስ ታጣቂ

ሰርጎ ገቦችን ለመከላከል... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ለስንዴ ግዢ ይወጣ የነበረን ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማዳን ተችሏል

## የሴክተሩ ተሃድሶ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ማበርከቱ ተነገረ

ገመቹ ከድር

አዲስ አበባ፡- በግብርና ሴክተሩ ላይ ተግባራዊ የተደረገው ተሃድሶ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ጉልህ ሚና ማበርከቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። ሚኒስቴሩ ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚያስፈልግ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ስንዴ ግዥ ማዳን መቻሉንም ገልጿል።

የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ኡመር ሁሴን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሴክተሩ የተደረገው ተሃድሶ ከለውጡ በፊት የነበሩ ችግሮችን በመለየት በሴክተሩ ተግባራዊ በተደረገው ተሃድሶ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ጉልህ ሚና አበርክተዋል። በተገኘው ውጤት ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚያስፈልገውን የስንዴ ምርት ፍላጎት በመሸፈን በሚቀጥለው ዓመት ስንዴን ወደ ውጭ አገር ለመላክ የሚያስችል ቁመና ላይም ተደርሷል።

ከለውጡ በፊት ለ27 ዓመታት በተግባር ያልታገዘ ግብርና መር ኢኮኖሚ እና በመኸር ግብርና ላይ ብቻ የተመሠረተ ግብርና ምርትና ምርታማነትን እንዳይጨምር አድርጓል ያሉት አቶ ኡመር፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት ተግባራዊ በተደረገው ተሃድሶ ሥራ በሴክተሩ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እየተመዘገበ ይገኛል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የሚያስችሉ በመኸር ግብርና ላይ ብቻ የተመሠረተውን በመቀየር የበጋ መስኖ ላይ ትኩረት ተደርጎ እንዲሠራ ተደርጓል። በዚህም በበጋ መስኖ እና መኸር ግብርና ስንዴ በማምረት ለአገር ውስጥ ፍጆታ የስንዴ ምርት ፍላጎት መሸፋን ተችሏል። አሁን የተገኘውን ስኬት መሠረት በማድረግ በሚቀጥለው ዓመት የስንዴ ምርት ወደ ውጭ አገር ለመላክ በትኩረት እየተሠራበት ነው።



አቶ ኡመር ሁሴን

ከዚህም በተጨማሪ ሴክተሩ በሁሉም ዘርፍ ምርትና

የሴክተሩ ተሃድሶ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል













## «አገራዊ ምክክሩ የሀሳብ ልዩነቶታችን የልማት እንጂ የጦርነት ምንጭ እንዳይሆኑ የሚያስችለን ነው»

-ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር

4ኛ ገጽ








# ‹‹አገራችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ተወዳዳሪ እንድትሆን ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን እውቅና መስጠት ያስፈልጋል››

**-አቶ አባዱላ ገመዳ**
**የኦሮሚያ ልማት ማኅበር የቦርድ ሰብሳቢ**

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዳማ፡- አገራችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ተወዳዳሪ እንድትሆን ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን እውቅና መስጠትና መሸለም እንደሚያስፈልግ የኦሮሚያ ልማት ማኅበር (ኦልማ) የቦርድ ሰብሳቢ አባዱላ ገመዳ አስታወቁ፡፡

የኦሮሚያ ልማት ማኅበር (ኦልማ) በትናንትናው ዕለት በአዳማ ከተማ ትምህርታቸውን ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል በኦሮሚያ አዳሪ ትምህርት ቤት ተከታትለው ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲ በከፍተኛ ነጥብ ለተመረቁ ተማሪዎች እውቅና ተሰጥቷል፡፡

በእውቅና አሰጣጡ ሥነሥርዓቱ ላይ የተገኙት የኦሮሚያ ልማት ማኅበር (ኦልማ) የቦርድ ሰብሳቢ አባዱላ ገመዳ እንደገለጹት፣ ተማሪዎችን መሸለምና እውቅና መስጠት ዩኒቨርሲቲ ለሚገቡ ተማሪዎች ትልቅ ጉልበትና አቅም ይፈጥራል። እንዲሁም አገራችን ከተቀረው ዓለም ጋር በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ተወዳዳሪ እንድትሆን ያደርጋል ብለዋል፡፡



እንደ ቦርድ ሰብሳቢው ገለጻ፤ እውቅና የተሰጣቸው ተማሪዎች ስድስት ወንድና አምስት ሴቶች ሲሆኑ ከአመታት በፊት ከሚማሩበት ትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት አምጥተው ወደ ኦሮሚያ አዳሪ ትምህርት ቤት የተቀላቀሉ ናቸው።ከአዳሪ ትምህርት ቤቶች ወደ ዩኒቨርሲቲዎች የተቀላቀሉ ተማሪዎች ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በከፍተኛ ውጤት እየተመረቁ ነው። ወደፊትም አገርን በከፍተኛ ደረጃ ይጠቅማሉ ተብሎ ይጠበቃል። በቀጣይ ጥሩ ውጤት የሚያስመዘግቡ ተማሪዎችን ለአገር ምሰሶ እንዲሆኑ በማሰብ ይህን መሰል የዕውቅናና ሽልማት ፕሮግራም ይቀጥላል፡፡

አገራች በሁሉም መስክ ከተቀረው ዓለም ጋር እንድትወዳደር አዳጊ ተማሪዎችን መርዳት ይገባል ያሉት አቶ አባዱላ፤ አገራችን በሳይንስና ቴክኖሎጂ እንድትበለጽግ ምሰሶ ይሆናሉ። እንዲሁም በኢትዮጵያ ለሚማሩ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ተማሪ ዎች ጥሩ አርአያ ይሆናሉ ሲሉ አስገንዝበዋል። ተማ ሪዎች የተሸለሙት ወደ ኦልማ ሲቀላቀሉ ነው፤ ጥሩ ደረጃ እንዲደርሱ የኦሮሞ ማኅበረሰብ ጤፍና ሰንጋ እያመጣ ሲደግፍ እንደነበር ገልጸው አመስግነዋል፡፡

ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ተማሪዎችን ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑ ማበረታታትና ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የገለጹት ቦርድ ሰብሳቢው፤ በቀጣይ ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚቀላቀሉ ተማሪዎች በብርታት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ያግዛል። ተማሪዎች በውጭ ባሉ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲማሩ በማመቻቸት የሚያገኙትን እውቀትና ልምድ ይዘው ወደ አገር በመመለስ ወገናቸውን እንዲያገለግሉ ይደረጋል ብለዋል፡፡

የኦሮሚያ ልማት ማኅበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ደጀኔ ኢቲቻ በበኩላቸው፤ እውቅናና ሽልማት የተሰጣቸው ተማሪዎች አስራ አንድ ሲሆኑ የብር፣ የዋንጫና የሜዳሊያ ሽልማት ተደርጎላቸዋል ብለዋል። ተማሪዎችን መሸለም ለቀጣይ ትውልድ ኃይል መስጠት ነው። በኦሮሚያ አዳሪ ትምህርት ቤት ተምረው ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች በቀጣይ ለአገር ትልቅ ሥራ መሥራት ይችላሉ። በተለይ ቴክኖሎጂን ተጠቅመው እንደ አገር ላሉ ችግሮች መፍትሔ ያበጃሉ።እንዲሁም ጥሩ ውጤት የሚያስ መዘግቡ ተማሪዎችን ማበረታታት እንደሚቀጥሉም አስታውቀዋል፡፡



ብርጋዴር ጀኔራል ነቢል አብደላ

## ሱዳን የትኛውም የታጠቁ ኃይሎች በሁለቱ አገራት መካከል እንዳይንቀሳቀሱ መወሰኗን አስታወቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሱዳን የትኛውም የታጠቁ ኃይሎች በሁለቱ አገራት መካከል እንዳይንቀሳቀሱ መወሰኗን የአገሪቱ መከላከያ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የሱዳን መከላከያ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ብርጋዴር ጀኔራል ነቢል አብደላ በሰጡት መግለጫ፤ በሁለቱ አገራት መካከል ጥብቅ ቅንጅት በማድረግ የዓለም አቀፍ የድንበር ቁጥጥር እንዲጠናከርና የትኛውም የታጠቁ ኃይሎች በሁለቱ አገራት መካከል እንዳይንቀሳቀሱ መወሰኑን አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያና የሱዳን አመራሮች በድንበር አካባቢ ለተቀሰቀሰው ውጥረት «አፋጣኝ እና ዘላቂ» መፍትሔ ለማበጀት የጀመሩትን ውይይት መነሻ እንደሆነ በተገለጸው የሱዳን ውሳኔ መሠረት የተዘጋው ድንበርም ከትናንት ጀምሮ እንዲከፈት መወሰኑም ተገልጿል።

ሁለቱን አገራት የሚያዋስነውና በገላባት እና መተማ መካከል የሚገኘው የኢትዮጵያ እና የሱዳን የድንበር ኬላ ከትናንት ጀምሮ በጄነራል አብዱል ፋታህ አል-ቡርሃን የሚመራው የሱዳን የጸጥታ እና መከላከያ ምክር ቤት ክፍት እንዲደረግ መወሰኑንም ሱዳን ገልጻለች።

የሱዳን መንግሥት መግለጫ አያይዞም፤ «ዕውቅና ባለው ሕጋዊ አሠራር መሠረት የገላባት ድንበር ማቋረጫ በሁለቱ አገራት መካከል እንቅስቃሴ እንዲኖር በሚል ከትናንት ጀምሮ እንዲከፈት ተወስኗል» ብሏል።

## ባለሥልጣኑ በዘጠኝ ዐብይ የደምብ መተሳለፍ ተግባራት 32 ሚሊዮን ብር ቅጣት መሰብሰቡን ገለጸ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደምብ ማስከበር ባለሥልጣን በአስራአንድ ወራቱ በዘጠኝ ዐብይ የደምብ መተላለፍ ተግባራት ከ32 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰቡን አስታወቀ።

በከተማዋ 121 ወረዳዎች 121 የአቅመ ደካማ ቤቶችን ለማደስ በእቅድ ይዞ እየሠራ ነው።

የባለሥልጣኑ የደምብ ጥሰት ክትትል ቁጥጥር እና እርምጃ አወሳሰድ ዘርፍ ምክትል ኃላፊ አቶ ደሳለኝ ፉፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፣ በከተማዋ የሚከሰቱ ሕገወጥ ተግባራትን ከጥንስሱ ለማጥፋት ባለሥልጣን መስሪያቤቱ በዘጠኝ ዐብይ የደምብ መተላለፍ ተግባራት ላይ በማተኮር ሰፊ የሪፎርም ሥራ እየሠራ መሆኑ ጠቁመዋል።



አቶ ደሳለኝ ፉፋ

በ11 ወራት በዘጠኝ ዐብይ የደምብ መተላለፍ ዓይነቶች 340 ሺህ 570 ሕገወጥ አድራጊዎችን በመለየት 338 ሺህ 70 በሚሆኑት ሕገወጦች ላይ እርምጃ መወሰዱን አሳውቀዋል።

እርምጃ ከመውሰድ ባሻገር ከቅጣት ገቢ 32 ሚሊዮን ብር ከሕገወጥ አድራጊዎች ላይ የተሰበሰበ ሲሆን የነበረውን ሕገወጥ ድርጊት በመቀልበስ ወደነበረበት የመመለስ ሥራ መሠራቱን ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደምብ ማስከበር ባለሥልጣን በክረምት ወራቱ መርሃ ግብሩ እቅድ የመንገድ ደህንነትን ከመጠበቅ አንጻር የሕገወጥ ጎዳና ላይ ንግድ በመከላከል መቆጣጠርን የክረምቱ ዋና ሥራችን ነው ብለዋል።

ሕገወጦች የእግረኛ መንገድ በመዝጋት እና ትራፊክ መጨናነቅ እና የመኪና ፍሰት ላይ የማስተካከል ሥራ በትኩረት የሚሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ሜክሲኮ አካባቢ ልደታ እና ቂርቆስ ክፍለ ከተሞችን በማስተባበር አካባቢው እንዲጸዳ እና ለማናቸውም ዓይነት ሕገወጦች ምቹ እንዳይሆን ተደርጓል ብለዋል። በዚህ መነሻነትም መገናኛ አካባቢ ያለውን አደባባይ የማጽዳት እና ከዚህ የተገኘውን ተሞክሮም ትላልቅ አደባባዮች ላይ የማስፋፋት ሥራ የሚሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

በክረምት መርሃግብሩ በግንባታ ሥራዎች የተለያየ መንገድ ተረፈምርቶችን መንገድ ላይ በመጣል መንገድ የሚዘጉ አካላትን ቀድሞ የመከላከል የመቆጣጠር እና እርምጃ የመውሰድ ሥራ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ባለሥልጣኑ በክረምት ወራቱ በከተማዋ 121 ወረዳዎች 121 የአቅመ ደካማ ቤቶችን ለማደስ በእቅድ ይዞ እየሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

በጉለሌ ክፍለ ከተማ የ11፣ በአቃቂ አምስት እና በአዲስ ከተማ ክፍለከተሞች የአቅመደካማ ቤቶች ተለይቶ ከወዲሁ እድሳት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደምብ ማስከበር በሕገወጥ መንገድ መሬት የሚይዙትንና በሕገወጥ መንገድ ቤት የሚገነቡት ላይ እርምጃ እንደሚወስድ ሁሉ ሕጋዊ ሆነው ቤት መገንባት ያቃታቸውን እና በተለያየ መንገድ አቅማቸው የደከመውን ታሳቢ በማድረግ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው ብለዋል።

የከተማዋ ደምብ ማስከበር በሕጋዊ መንገድ ግንባታ የሚያከናውኑት ጋር የማይደርስ መሆኑን የገለጹት ነገር ግን ከሚመለከተው አካል ሕጋዊ መነሻ ሳይኖራቸው ግንባታ የሚያካሂዱ አካላት ላይ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን አመላክተዋል።

ኅብረተሰቡ በከተማዋ የሚመለከታቸውን ሕገወጥ ድርጊቶች ሲመለከት በነፃ ስልክ ቁጥር 9995 ጥቆማ እንዲሰጥ ጥሪ አቅርበዋል።

እንደ አቶ ደሳለኝ ፉፋ በከተማዋ ደምብ ማስከበር የሪፎርም ሥራ ሕገወጥ፤ የመሬት ወረራ፣ መሬት ማስፋፋት፣ ግንባታ፣ የጎዳና እና በረንዳ ንግድ፣ ደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ፣ ሕገወጥ የእንስሳት እርድና ዝውውር፣ ሕገወጥ የመንገድ አጠቃቀም፣ አዋኪ ድርጊት እና በሕገወጥ ማስታወቂያዎች ላይ በማተኮር ይሠራል።

# «የኢንዱስትሪዎችን 48 በመቶ የማምረት አቅም ብክነት ለማሻሻል ትኩረት ሰጥተን እንሠራለን»

-አቶ መላኩ አለበል
የኢንዱስትሪ ሚኒስትር

**ውብሸት ሰንደቁ**

ድሬዳዋ፡- የኢንዱስትሪዎችን 48 በመቶ የሚጠጋ የሚባክን የማምረት አቅም ለማሻሻል ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሠራ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ገለፀ፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም እና በ2015 በጀት መነሻ ዕቅድ ላይ በድሬዳዋ ከተማ ትናንት ውይይት ሲካሄድ እንደገለፁት፤ በ2014 በጀት ዓመት ከነበሩ ከፍተኛ ተግዳሮቶች ጋር በመጋፈጥ የኢንዱስትሪዎችን ዝቅተኛ የማምረት አቅም በአማካይ 52 ነጥብ 7 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ ቀሪውን የኢንዱስትሪዎች 48 በመቶ የሚጠጋ የሚባክን የማምረት አቅም ማሻሻል የ2015 በጀት ዓመት ዋነኛ የትኩረት አጀንዳ ነው፡፡

በ2014 በጀት ዓመት የአምራች ኢንዱስትሪውን በማነቃቃት፤ ማምረት ያቆሙ ኢንዱስትሪዎችን ሥራ በማስጀመር እና በሥራ ዕድል ፈጠራ ረገድ አበረታች ድሎች መገኘታቸውን የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ በዘርፉ ለተገኙ ውጤቶች የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ትልቁን ድርሻ እንዳለውም ተናግረዋል፡፡

ንቅናቄው በስድስት ወራት ውስጥ በዘመናት ሊፈቱ ያልቻሉ የዘርፉ ችግሮች የተፈቱበት እና የተዘጉ ፋብሪካዎች እንዲከፈቱ ማድረግ የተቻለበት እንዲሁም የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት ለማሳደግ የተንቀሳቀስንበት ንቅናቄ ነውም ብለዋል፡፡

በተመሳሳይ ከዘርፉ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ግኝት ለማሳደግ በተሠራ ሥራም በጦርነት፣ በድርቅ እና በአሜሪካ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጠና (ከአግዋ)



በታገደችበት ሁኔታ አገሪቷ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዘርፉ 500 ሚሊዮን 44 ሺህ ዶላር ያገኘችበት የበጀት ዓመት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ገቢው ከአለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀርም የ28 በመቶ ብልጫ እንዳለው ገልጸዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ የገቢ ምርቶች በአገር ውስጥ ምርት መተካታቸውንም ሚኒስትሩ ጠቁመዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ከሁለት ሺህ 800 በላይ ኢንዱስትሪዎች ተቋቁመዋል ያሉት አቶ መላኩ፤ ከእነዚህ ውስጥ 77 ያህሉ ከፍተኛ፤ 816 መካከለኛ እና አንድ ሺህ 945 አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ናቸው ብለዋል፡፡ በኢንዱስትሪዎቹም ወደ 255 ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩንም ጠቁመዋል፡፡

ትልቁ አጀንዳችንም የሥራ ዕድል በመፍጠር የዜጎችን ሕይወት መቀየር ነው ያሉት ሚኒስትሩ አቶ መላኩ፤ የሥራ ዕድል ፈጠራን ሆነ ኢንዱስትሪዎችን የማስፋፋት ሥራ ሰላም እንደሚፈልግ አመልክተዋል፡፡

እንደ አቶ መላኩ ገለፃ፤ ብዙዎች በየአካባቢው እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮች ከአመራሩ ውጪ ያሉ ችግሮች ናቸው ተብለው ሊወሰዱ አይችሉም፡፡ በምንመራው ተቋምም ሆነ ማንኛውም ደረጃ ውጤት የማምጣትና ያለማምጣት፤ ችግር የመፍታትም ሆነ ያለመፍታት ጉዳይ በአመራሩ ላይ የሚጣል ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ለውጥ የሚመጣበት አካባቢ ሆነ ተቋም የአመራር ውጤት ነው፤ ለውጥ የማይመጣበት አካባቢ ሆነ ተቋም ደግሞ ከአመራር ችግር የሚመነጭ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ከድሬዳዋ ብዙ ልንማርና ተሞክሮ ልንወስድ ይገባል ያሉት ሚኒስትሩ፤ የድሬዳዋ ከተማ የነበረውን የፀጥታ ችግር በመቅረፍ ሙሉ በሙሉ ወደ ሰላም መግባቷን በአብነት አንስተዋል፡፡

የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ከድር ጀዋር በበኩላቸው፤ ሰላማችንን ማስጠበቅ በመቻላችን በድሬዳዋ አስተዳደር እና በፌዴራል መንግሥት ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተቀናጀ ሥራ የድሬዳዋ የኢንዱስትሪ ማዕከልነት ሊረጋገጥ ችሏል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

እንደ አቶ ከድር ገለፃ፤ በድሬዳዋ የተገነቡት ኢንዱስትሪዎች የድሬዳዋን የኢንዱስትሪ ማዕከልነት የሚያሳዩ ብቻ ሳይሆኑ ለአልሚውም ሆነ ለነዋሪው ብሩህ ተስፋን የፈነጠቁና ለከተማዋ ዕድገት የላቀ አስተዋፅዖ ያበረከቱ ናቸው፡፡ ኢንዱስትሪዎቹ በከተማዋ የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባሻገር ለአገራችን የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ረገድ ጉልህ ሚና እየተጫወቱ ነው፡፡




# በመተከል የተገኘው ሰላም ዘላቂነት እንዲኖረው እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በመተከል የተገኘው ሰላም ዘላቂነት እንዲኖረው በትኩረት እንደሚሠራ የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዱዓለም አስታወቁ።

«የጥላቻን ሥር እየነቀልን የፍቅር ችግኝ እንተክላለን» በሚል መሪ መልዕክት በመተከል ዞን የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ተካሂዷል።

በመርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዱዓለም መተከል ብዝኃነትን ይዞ ፍፁም ሰላምና ፍቅር የነበረበት ለሌሎች አርዓያ የሚሆን ዞን እንደነበር አስታውሰዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አገርን ለማፍረስ የሚጥሩ ኃይሎች መተከልን ኢላማ ማድረጋቸውን ጠቁመው፤ አካባቢው ብዝኃነት ያለበት፣ የሕዳሴ ግድብ ያለበት፣ ከሱዳን ጋር የሚያገናኝ በመሆኑ ጠላቶች ትኩረት እንዳደረጉበት ነው የተናገሩት።

ጠላቶች ባደረሱት ጥቃት ወገኖቻችንን አጥተናል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ዛሬ አካባቢው ወደ ቀደመው ክብሩ ተመልሷልም ሲሉ ገልጸዋል።

ሰላሙ በከፍተኛ መስዋእትነት መምጣቱንም አንስተው፤ የዛሬው ችግኝ ተከላ አንድም ኢትዮጵያን አረንጓዴ ማልበስ በሌላ በኩልም አብሮነትንና ፍቅርን መትከል ነው ብለዋል። በአካባቢው አሁንም ቀሪ ጠንካራ ሥራዎች እንደሚሠሩ አስታውቀዋል።

ወደ ቀያቸው የተመለሱት ወገኖች ተረጋግተው እንዲኖሩ መሥራት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ብናልፍ፤ የአካባቢው ሰላም ዘላቂ እንዲሆን የሰላም ሚኒስቴር ከሁለቱ ክልሎች ጋር በጋራ እንደሚሠራም አስገንዝበዋል።

የፌዴራል መንግሥትም የአካባቢው ሰላም በዘላቂነት እንዲቀጥል በትኩረት እንደሚሠራ ገልጸዋል።

በዚሁ ወቅትም የአማራ እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች በሁለቱ አዋሳኝ አካባቢ «የሰላም እና አብሮነት ፓርክ» ተብሎ በተከለለ ቦታ ላይ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም አካሂደዋል፡፡

የችግኝ ተከላው ዋና ዓላማ የሁለቱ ክልል ሕዝቦችን በልማት በማስተሳሰር የቆየውን አንድነት ከማስቀጠል ባለፈ በቀጠናው ያለውን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በደለል እንዳይሞላ ማስቻል እንደሆነ ተገልጿል።

የሰላምና ፀጥታ ጉዳይ ለልማት ሥራው እንቅፋት እንዳይሆን በልዩ ትኩረት እንደሚሰሩ ሲሉ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ተናግረዋል፡፡

በችግኝ ተከላ መርሐግብሩ ላይ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለ (ዶ.ር)፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርእሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሐሰን፣ የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዱዓለም፣ የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጄኔራል አቶ ተመሥገን ጥሩነህን ጨምሮ የክልል እና የፌዴራል ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

## በክረምቱ የጎርፍ አደጋ ሊከሰት ስለሚችል ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ኢንስቲትዩቱ አሳሰበ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው ክረምት ወቅት አዋሽ ተፋሰስን ይዞ አፋር፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ምሥራቃዊ የአገሪቱ ክፍሎች፣ በሰሜን ተከዜና ጣና፣ ጋምቤላ ባሮ አኮቦ አካባቢዎች የጎርፍ አደጋ የመከሰት ዕድሉ ሰፊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡ ከደቡብ አትላንቲክ እና ሕንድ ወደ አገራችን የሚገባ እርጥበታማ አየር በተጠናከረ መልኩ በሐምሌና ነሐሴ ወራቶች እንደሚቀጥልም ተመልክቷል፡፡

በኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት የአየር ትንቢያ እና ማስጠንቀቂያ ዳይሬክተር ወይዘሮ ጫሊ ደበሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢንስቲትዩቱ በተያዘው ክረምት ሊከሰት ከሚችል ጎርፍ አደጋ ኅብረተሰቡን ለመከላከል ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

በተያዘው ክረምትም በመጠንም በስፋት በተለያዩ አካባቢዎች መደበኛና ኢመደበኛ የሆነ ዝናብ ስለሚጠበቅ ኅብረተሰቡ ከጎርፍ አደጋ ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል ብለዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ክረምት ከመግባቱ በፊት ጀምሮ ኅብረተሰቡ ከጎርፍ አደጋ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የአየር ሁኔታ ትንበያ መረጃዎችን ሲሰጥ መቆየቱን አውስተው፤ በአሁኑ ጊዜም ከኢንስቲትዩቱ በተሰጠው አየር ትንቢያ መረጃ መሠረት ረጅም ሰዓታት እና ሙሉ ቀን የዝናብ መጠን በተለያዩ ቦታዎች እየተስተዋለ ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡ ሐምሌን ወር ጨምሮ በቀጣይ ሁለት ወራትም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚቀጥል ገልጸዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ጫሊ ገለጻ፤ ከደቡብ አትላንቲክ እና ሕንድ ወደ አገራችን የሚገባ እርጥበታማ አየር በተጠናከረ መልኩ እንደሚቀጥል ይጠበቃል፡፡ ይህን ተከትሎ ከፍተኛ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የአየር ትንበያው ያሳያል፡፡ ከዚህ አኳያ ኅብረተሰቡ ጎርፍ ሊከሰትባቸው የሚችሉ መንገዶችን ተረድቶ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

በተለይ በምሥራቅ አማራና በመካከለኛው ኦሮሚያ የሚዘንበው ዝናብ ወደ አዋሽ ወንዝ ስለሚገባ በአካባቢው የሚኖሩ ኅብረተሰብ ክፍሎች ጎርፍ መከላከያ ቦዮችን በመሥራትና ከባለሙያ በሚሰጠው ምክር መሠረት ጥንቃቄ እንዲያድርጉ መክረዋል፡፡

በተለይ፤ በወንዞችና በተዳፋትና ገደላማ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስበዋል፡፡

በዘንድሮው ክረምት መደበኛና ኢመደበኛ የዝናብ መጠን እንደሚኖር ጠቁመው፤ እስከ አሁን ባለው አየር ሁኔታ ትንቢያ መሠረት በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች መደበኛ እና ኢመደበኛ ዝናብ ተጠናክሮ ስለሚቀጥል ኅብረተሰቡ ከኢንስቲትዩቱ የሚሰጡትን መረጃዎች በመከታተል ከጎርፍ አደጋ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ መክረዋል፡፡

# «አገራዊ ምክክሩ የሀሳብ ልዩነቶታችን የልማት እንጂ የጦርነት ምንጭ እንዳይሆኑ የሚያስችለን ነው»

-ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የምናደርገው የሁሉንም ሀሳብ ያሳተፈ አገራዊ ምክክር ያለንን የሀሳብ ልዩነት ለአገራዊ ልማት እንጂ ለጦርነት ምንጭ እንዳይሆን የሚያስችለን እንደሆነ የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ገለጹ።

የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የባህል፣ የአኗኗር እና የሃይማኖት ብዝሃነት ያላት አገር ናት። በሁሉም አካባቢና ሕዝብ ዘንድ የተለያዩ አገራዊና ልማታዊ እሳቤዎች አሉን፣ ይኖሩናል። በቀጣይ በምናደርገው አገራዊ ምክክር መድረክ እነዚህን ሁሉ ሀሳቦች ያማከለ እና ያሉትን ልዩነቶች ሁሉ ለልማት እንዲውሉ ያስችለናል።

ኮሚሽኑ በአሁኑ ወቅት ለምክክር መድረኩ የሚያስፈልጉ ተግባራትን እየሠራ መሆኑን የተናገሩት ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን፤ በኢትዮጵያ ታጥቶ የነበረው ሁሉን አቀፍ ሰላምና ልማት እንዲረጋገጥ ታስቦ የሚደረገው አገራዊ የምክክር መድረክ ላይ በሕዝቦች መካከል ያሉት የሀሳብ ልዩነት ለሰላም፣ ልማትና ብልጽግና ማሳላጫነት እንዲውሉና በተቃራኒው ለግጭትና ለጦርነት ምንጭ እንዳይሆኑ ለማስቻል መሠራት ያለበትን እንየሠራን ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ ሁሉንም የሀሳብ ልዩነቶች አሳትፈን በመመካከርና በመወያየት እንደ አገር አገራዊ ልማትና ብልጽግና እንዲፋጠኑልን መሥራት ያለብንን ሥራ ሁሉ እንሠራለን ብለዋል ፕሮፌሰር መስፍን።

የሚካሄደው የምክክር መድረክ ሕዝቡ በራሱ አብሮነቱን በማስቀጠል አገራዊ ታሪክ የሚሠራበት እንደሆነም ኮሚሽነሩ አክለው ተናግረዋል።

እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ገለጻ፤ የምክክር ሂደቱ ሁሉም በእኩልነት ሀሳቡን አውጥቶ ተነጋግሮ ለአገር ልማትና እድገት የሚበጅ መሠረት የሚጥልበት ነው። በአብሮነታችን የሀሳብ ልዩነት በመኖሩ ብቻ ግጭቶች እንዳይፈጠሩ የሚያደርግ፣ መወያየትን፣ በመጋገርን፣ ልዩነትን ወደ የለውጥ ማምጫ መሣሪያነት የመጠቀምን አቅም የምናሳድገበት የምክክር መድረክ ነው።



ምክክሩ ሁሉም በእኩልነት ሀሳቡን የሚያቀርብበት ነው ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፤ ለአገር እድገትና ብልጽግና የሚበጁ ሀሳቦች የሚፍልቅበት እንደሆነም ጠቁመዋል።

ፕሮፌሰር መስፍን አክለውም፣ ምክክሩን አድርገናል ለማለትና ለይስሙላ የምናደርገው አይደለም። የለይስሙላ አገራዊ የምክክር መድረኮች በአገራችን ታሪክ ውስጥ በደርግና በሕወሓት ዘመንም ተደርገዋል፣ በቀጣይ ሊደረግ የታሰበው ግን ከነዚህ በተለየ ሁኔታ ዘላቂ ውጤት በሚያመጣ መልኩ ሃሳቦች በነፃነት የሚነሱበት ይሆናል።

የመማከሪያና መወያያ ሀሳቦቹ የሚመነጩትና የሚፈልቁት ከራሱ ከሕዝቡ መሆኑና የሁሉም ነገር ባለቤት እራሱ ሕዝቡ መሆኑን የገለጹት ፕሮፌሰር መስፍን፤ ትግበራው በታለመለትና በተነገረው ልክ እንዲሄድ ኮሚሽኑ ጠንክሮ እየሠራ መሆኑ ተናግረዋል።

ምክክሩና ውይይቱ በአገሪቱ ባሉት አንድ ሺህ 300 ወረዳዎች ሁሉም ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ነው ያሉት ፕሮፌሰሩ፣ የሰላም መደፍረስና ግጭቶች በሚስተዋሉባቸው አካባቢዎችም ጭምር ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በማስተሳሰር የውይይት ሂደቱን ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

## ሰርጎ ገቦችን ለመከላከል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ቡድን ጋር በጥምረት በከፈቱት ተኩስ በሰው ሕይወትና በንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል፡፡

ሆኖም የአገር መከላከያ ሰራዊት፣ የክልሉ ፖሊስና ሚሊሻ እንዲሁም የአዋሳኝ አካባቢዎች ርብርብ በማድረግ ቡድኑን መከላከል ብቻ ሳይሆን መደምሰስ ተችሏል፡፡ አሁን ላይ በክልሉ ሰላም ቢሰፍንም አስተማማኝ ደረጃ ለማድረስ በተለይ ሰርጎ ገቦችን ለመከላከል በጥምረት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ሸኔ ከኦሮሚያ አልፎ በክልሉ የሚንቀሳቀስ ታጣቂ ኃይል ጋር በጋምቤላ ጥቃት ይፈጽማል የሚል ጥርጣሬ እንዳልነበረ የተናገሩት አቶ ፒቴር፣ ከተከሰተው ችግር ትምህርት በመውሰድ ከክልሉ የሚዋሰኑ እንደ ደምቢ ዶሎ፣ አንፍሎ፣ ኢሉ አባቦር ዞን ጋር የተጀመረውን የጥምረት እንቅስቃሴ በማጠናቀር ከደቡብ አዋሳኝ አካባቢዎች ጋር ለመሥራት እቅድ እንዳለ አመልክተዋል፡ ፡

ከአካባቢዎች ጋር በጥምረት እየተሠራ ያለው ሥራ ሰርጎ ገቦችን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን ወንጀል ሰርተው የተደበቁ ሰዎችንም በመለየት ለሕግ ለማቅረብ እንደሚረዳ የገለጹት አማካሪው፣ በተለይ ደምቢ ዶሎና አንፍሎ ጋር በሁለቱ በኩል ያሉ የጸጥታ አካላት ተናበው በሠሩት ሥራ ጥሩ ውጤት መገኘቱን ጠቅሰዋል፡፡

በክልሉ ያሉ የሱዳን ስደተኞች ተመሳስለው ለአካባቢው ታጣቂዎች በድብቅ ጦር መሣሪያ እያቀረቡ ያሉ ሕገ ወጦችን ለመከላከል የኢትዮጵያ መንግሥት ከሱዳን መንግሥት ጋር በቅርብ ጊዜ የግንኙነት መድረክ ማቀዱን የጠቆሙት አቶ ፒቴር፣ በተመሳሳይ መልኩ በኢትዮጵያ የተጀመረውን የአረንጓዴ አሻራ በሱዳንም ለመተግበር ኦሮሚያ፣ ጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ የጋራ ኮሚቴ በማቋቋም በሱዳን ችግኝ ለመትከል በመንግሥት በኩል መታቀዱን አንስተዋል፡፡

በክልሉ ተፈጥሮ የነበረው የጸጥታ ችግር ሁለቱ ታጣቂ ኃይሎች የተላላኪነት ሚና ቢጫወቱ የሴራው አቀነባባሪ ሕወሓት መሆኑ ግልጽ ነው ያሉት አቶ ፒቴር፣ ዓላማው ደግሞ ክልሉን በማወክ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ የልማት ሥራዎችን በማደናቀፍ የውጭ ኃይሎችን ለማስደሰት መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

እንደ አቶ ፒቴር ማብራሪያ፣ በወቅቱ ከተፈጠረው ችግር ጋር ተያይዞ የጠፋ የሰው ሕይወት፣ የወደመና የተዘረፈው ንብረትና ስነልቦናዊ ቀውስ የሚያጣራ ቡድን ተቋቁሞ በቅርቡ ሥራ ይጀምራል፡፡ ጥይት ዘመድን ስለማይለይ በተደረገው የተኩስ ልውውጥ ንጹሃን ዜጎች ተጎድተው ይሆናል፡፡ የዝርፊያ እንቅስቃሴዎችም ነበሩ፡፡

በተለይ ችግር በመፍጠር የኦሮሞና የጋምቤላን ሕዝብ ለማጋጨት የተኬደው ርቀት ቀላል ባይሆንም ከአገር ሽማግሌዎችና ከክልሉ የጸጥታ አካላት ጋር በጥምረት በመሠራቱ የጠላቶችን ሴራ ማክሸፍ መቻሉንም አቶ ፒቴር አክለው ገልጸዋል፡፡

## ጠቅላይ ምክር ቤቱ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሰላምና ልማት ወሳኝ ጉዳዮቻችን ናቸው ያሉት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም፤ በዚህ ረገድ ሳንከፋፈል አንድነታችንን ጠብቀን መጓዝ ይኖርብናል። አዲሱን ኃላፊነት ስንረከብ በመፈቃቀርና በመከባበር ላይ በተመሠረተ አግባብ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል። ተለያይተን ሳይሆን ተቀራርበን ለመጓዝ ዝግጁ ነን። በሥራ ዘመናችን ለመላው ሙስሊም ኅብረተሰብና ለሰላም ወዳድ ኢትዮጵያውያን በቻልነው ሁሉ በጎውን ለማድረግ ጥረት እናደርጋለን ብለዋል።

በይፋ ሥራ መጀመራችንን ስናበስር በታላቅ ደስታ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በቀሪው ዘመናችን አንድነታችንን አጠናክረን የተሳካ ጊዜ እንደምናሳልፍ ዕምነት አለኝ ሲሉ ተናግረዋል። በምክትል ፕሬዚዳንትነት የተመረጡት ሼህ አብዱልከሪም ሼህ በድረዲን በበኩላቸው፤ ከሁሉ በፊት ቅድሚያ የምንሰጠው ለአገራችን ሰላም ነው። በሰላም ጉዳይ ላይ አንደራደርም ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት እንዲጠናከር አቅም በፈቀደው ሁሉ ጥረት እናደርጋለን፤ ለዚህም ጥረታችን ሕዝብ ሙስሊሙም ሆነ መላው ሕዝብ ከጎናችን እንደሚቆም አንጠራጠርም ሲሉ ተናግረዋል።

ሃብታሙም ደሃውም ፣ ወንዱም ሆነ ሴቱ ማኅበረሰብ ለልማቱም ሆነ ለሰላሙ መረጋገጥ ግንባር ቀደም ሆኖ መገኘት አለበት ያሉት ሼህ አብዱልከሪም፤ የጠቅላይ ምክር ቤቱ አመራሮችም ለዚሁ ተግባር ግንባር ቀደም ሆነው ለመሥራት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል። መኮራረፍን ሳይሆን መግባባትንና አንድነትን ነው የምንፈልገው። በዚህ አግባብ ችግሮች ቢኖሩ እንኳን ሁሉም ሳይገፋፋ በሰላማዊ መንገድ ችግሮችን የሚፈቱበትን መንገድ እናመቻቻለን ብለዋል።

በመሆኑም ሙስሊሙ ኅብረተሰብ ለጋራ ሰላሙ እጅ ለእጅ ተያይዞ ከምክር ቤቱ ጎን ሊሠራ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። በጉባዔው የተመረጡ አመራሮችና 14 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት መጅሊሱን እንደሚመሩ ታውቋል።

## የሴክተሩ ተሃድሶ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ምርታማነትን ለመጨመር ግብርና ዘርፉን የማዘመን ሥራ ሠርቷል፡፡ እስከ አሁን ድረስ በተሠራው ሥራ ከ550 በላይ የሚሆኑ ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች ከግብር ነፃ ግዥ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል ብለዋል፡፡

ከዋጋ ግሸበት ጋር በተያያዘም የማዳበሪያ ዋጋ ንረትን ለመከላከል ለአርሶ አደሩ 25 ፐርሰንት ድጋፍ መደረጉን አስታውሰው፣ ማዳበሪያ እና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ረገድ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመቅረፍ በዘርፉ ምርምር ከሚያደርጉ አካላት ጋር በመሥራት አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ነው ብለዋል፡፡

አካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዘ አትክልትና ፍራፍሬ ምግብ ዋስትና በሚያረጋግጥ መልኩ ከአረንጓዴ አሻራ ጋር በማጣመር ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እየተሠራ እንደሆነም ሚኒስትሩ ጠቁመዋል፡፡

አረንጓዴ አሻራ የአየር ንብረት ለውጥ በመከላከል ትልቅ አስተዋጽዎ አለው ያሉት ሚኒስትሩ ያለውን ክረምት አርሶ በጋ መቀመጥ ባህልን በመቀየር ጠንክረን ከሠራን ወደ ካርቦን ገበያ ለመሸጋገር ሰፊ ዕድል መኖሩን ገልጸዋል፡ ፡

ሚኒስቴሩ ጸጥታ ችግር ባለበት ቦታ ሁሉ ግብርና ሥራ እንዳይስተጓጎል ከጸጥታ አካላት እየሠራ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ እስከ አሁን ድረስ በተሠራው ሥራ አብዛኛው ጸጥታ ችግር ያለባቸው ቦታዎች ወደ ግብርና ሥራ መግባታቸውን ጠቅሰው፣ ግብርና ግብዓቶችም እየደረሳቸው ይገኛል ብለዋል፡፡

ወጣቱና ሚዲያው በዚህ ረገድ ኅብረተሰቡን በማነሳሳት ውጤት ሊያመጡ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ እንዲሠሩም ሚኒስትሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ያሸነፈችውም፣ የምታሸንፈውም ኢትዮጵያ ናት!

ኢትዮጵያ መልከ ብዙ ናት፤ ይህ በብዝሃነት የደመቀው ገጿ ውበትን ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ መድረኮች ከፍ ያለ ክብርና ሞገስን ያስገኘላትን የአሸናፊነት ካባ ሲያጎናጽፋት ኖሯል፤ እያጎናጸፋትም ይገኛል። ብዙዎች ብዝሃነታቸው ውበትን ሳይሆን የመከፋፈል ስሌትን ሲያቀብላቸው፤ ሕብረ ብሔራዊነታቸው በአንድነት ቆሞ ማሸነፍን ሳይሆን ተከፋፍሎ ለየብቻ በመቆም መውደቅን ሲቸራቸው ተመልክተናል። ይህ አካሄድ ምናልባት የራሳቸው ኑባሬ ሳይሆን፤ ከውጪ ከፋፍለው ሊጥሏቸው ያለሙ ኃይሎች ስሌት ውጤት ሊሆን እንደሚችል ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ መመልከቱ እውነቱን ለመረዳት ሕያው ማሳያ ነው።

እንዴት ቢሉ፤ ኢትዮጵያ ለዘመናት የኖረው አንድነቷንና ገናንነቷን አስጠብቃ፣ ከነ ክብሯና ሉዓላዊነቷ እንድትዘልቅ፤ ከራሷም አልፋ ለመላው ጭቁን ጥቁር ሕዝብ አብነት ሆና እንድትገለጥ ያደረጋት ሃቅ ነው። ይህ ሃቅ ያልተዋጠላቸው እና የዘመናት የሴራ ጉዟቸው ያልሰመረላቸው የውስጥና የውጭ ጠላቶቿ ግን፤ አንድነቷን በልዩነት ለመተካት፤ በህብር የጠነከረ ክንዷን ለማለዘብ ያልቆፈሩት ጉድጓድ፤ ያልሞከሩት የከፋት ተግባር አልነበረም። ሆኖም ኢትዮጵያዊነት ከምንም ነገር በላይ ነውና ሴራቸው ሳይሰምር፤ ክፋታቸው ግቡን ሳይመታ ትናንትን ተሻግራ ዛሬ ከነክብሯ ተገልጣለች። ዛሬንም አልፋ ነገ ከከፍታዋ ሰገነት ልትቀመጥ ጉዞዋን ቀጥላለች።

ለዚህ በክብር ያጌጠ፤ በአሸናፊነት ለደመቀ አገራዊ ጉዞ ደግሞ ውብ ኢትዮጵያን የፈጠረው የብዝሃነት ገጿ መከሰቻ የሆኑት ጀግኖች ልጆቿ ገድል በየዘመናቱ በየፈርጁ ሲገለጥ ኖሯል። ለነጻነቷ በጦር አውድማ ተዋድቀው በደማቸው ያጸኗትን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገውላታል። በደም የደመቀው ሰንደቋ በድህነት ዝቅ እንዳይል ለኢኮኖሚዋ በልማት ጎዳናው ዛሬም ልጆቿ ይተጉላታል። ሰንደቋ በዓለም አደባባይ ከፍ ብሎ እየተውለበለበ እንዲከበር፣ ኢትዮጵያዊ ማንነት እንዲዘከር የሚያደርጉ የስፖርቱ ዘርፍ በተለይም አትሌቶች በላባቸው በሚያስመዘግቡት ድል ኢትዮጵያውያንን የሳግ እንባ አራጭተዋል። የዚህ ሁሉ ማሰሪያው፤ የድሎች ሁሉ ማሳረጊያውና የሕዝቦች ታላቅነት ማረፊያው ደግሞ የኢትዮጵያን አሸናፊነት ማረጋገጥ ነው።

ኢትዮጵያውያን በየመድረኩ ኢትዮጵያን በአሸናፊነት ሰገነት ላይ ለማኖር ሲዋደቁ ግላዊ ማንነታቸው ወይም የብሔር ጥግ እሳቤያቸው ገፍቷቸው አይደለም። ይልቁንም ኢትዮጵያዊነት ከራስም፣ ከብሔርም በላይ መሆኑን ተገንዝበው እንጂ። ለዚህም ነው በዓድዋ ተራሮች ያለ ልዩነት በአንድ ሞተው ነጻነትን የተጎናጸፉት፤ ለዚህም ነው የሕዳሴውን ግድብ በጋራ ገንብተው ለዘመናት የናፈቁትን ከዓባይ ወንዝ ብርሃን የማየት ሕልማቸውን እውን ያደረጉት፤ ለዚህም ነው አትሌቶቻችን ከግል ክብራቸው ይልቅ ለአገር ክብር ቅድሚያ ሰጥተው በቡድን ታግለው በማሸነፍ ሰንደቋን ከሃያላን አገራት በላይ ከፍ አድርገው እያነቡ ኢትዮጵያውያንን የደስታ እንባ የሚያራጩት።

ዛሬም በ18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ እየሆነና እየተመለከትን ያለነው ይሄንን እውነት ነው። አትሌቶች ከራስ ይልቅ ለሃገር፤ ከብሔር መሳሳብ ይልቅ ለኢትዮጵያዊነት ክብር አንገት ለአንገት ተናንቀው ሲፋለሙ፤ ከፍ ባለ ኢትዮጵያዊነት ወኔ ድል ሲያደርጉ፤ ስለ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ሲያለቅሱና ሲስቁ ታይተዋል። ይህ ኢትዮጵያ ትናንትም ሆነ ዛሬ በልጆቿ ብርቱ ትግል እያሸነፈች ያለች መሆኑን በወጉ የሚያስረዳ ከመሆኑም በላይ፤ ለኢትዮጵያውያን ትልቅ የከፍታን ሕልም የሚያሲዝ፤ ለጠላቶቿ ደግሞ ሌላ የሙሾ ዘመን የሚፈጥር ሆኖ እየተገለጠ ያለ ነው።

ይሁን እንጂ ጠላቶቿ (በውስጥም በባንዳነት ያሉት፤ በውጭም በአዛዥነት የቆሙት) ዛሬም ይሄን እውነት አምነው ለመቀበል ሲቸገሩ ይታያል። ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ዝቅ አድርጎ ብሔርና ግለሰብን ለማንገስ፤ ከቻሉም በግለሰቦች ላይ ፍላጎታቸውን በመጫን ድብቅ አጀንዳቸውን በእነሱ ላይ ተረማምደው ለማስፈጸም መፍጨርጨራቸው አልቀረም። ይህ ትናትን የነበረ፤ ዛሬም ያለ፤ ነገም ሊቀጥል የሚችል የሴረኞች እኩይ መስመር ነው። ሆኖም ትናንትም አላሸነፈም፤ ዛሬም ማሸነፍ አልቻለም፤ ነገም የሚሳካ አይሆንም።

በአንጻሩ ሚስማር ሲመቱት እንደሚጠነክር ሁሉ፤ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ፈታኞች በበዙበት ቁጥር በአሸናፊነት መውጣቱን መንገዱ አድርጎ ዘልቋል። ምክንያቱም ኢትዮጵያዊነት የግለሰቦች ወይም የጥቂት ቡድኖች ጉዳይ ሳይሆን፤ አገርን አሸናፊ የማድረግ እውነት ነው። በ18ኛው የዓለም ሻምፒዮናም እየሆነና እየተገለጠ ያለው ይሄው ሃቅ ነው። እናም በየትኛውም መስክ ኢትዮጵያውያን ሲያሸንፉና ሰንደቅ ዓላማቸውን ከፍ ሲያደርጉ የምታሸንፈው መልከ ብዙዋ ኢትዮጵያ ናት። ለዚህም ነው ያሸነፈችውም፣ ወደፊት የምታሸንፈውም ኢትዮጵያ ናት ማለታችን!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::**

## ሌብነት ላይ የተመዘዘው ሰይፍ እንዳይመለስ

**ቦጋስ አበበ**

ሰሞኑን በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የሰማነው የሙስና ቅሌት ጆሮን ‹‹ጭው›› የሚያደርግ ነው። በእርግጥ ከዚህ ቀደም በተለያየ ጊዜ ከአሁኑ የባሰም የሙስና ቅሌት በዚህች ድሃ አገር እንደተፈጸመ እናስታውሳለን። ይህኛውን የተለየ፣ ከባድ እና እጅግ አስደንጋጭ ያደረገው አገር በጦርነትና በግጭቶች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቿ ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው የእለት ጉርሳቸውን ከሌሎች እጅ በሚጠብቁበት በዚህ ወቅት በሰብአዊ ተግባር ላይ በተሰማራ ተቋም ውስጥ መፈጸሙ ነው።

በብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የተፈጸመው ከባድ ሌብነት ፣ሌብነት ብቻ ነው ብሎ ለማሰብ የሚከብድ ነው ፣ ሰብአዊ እርዳታ በሚጠብቁ ሚሊየኖች ላይ የተፈጸመ ሰብአዊ ወንጀል ጭምር ነው። ተቋሙ በፈጠረው ወንጀል ምክንያት የሚልሱት የሚቀምሱት አጥተው ሕጻናት ሳይቀሩ እስከ ህልፈተ ህይወት ዋጋ ከፍለው ሊሆን ስለሚችል ቅሌት በቀላሉ መታየት የለበትም።

ይህን ጸያፍ በደል በአገርና በሕዝብ ላይ የፈጸሙ ግለሰቦች ሌቦች ብቻ አይደሉም። አገርን ከጀርባዋ ከሚወጉ ባንዳዎች ተለይተው የሚታዩ አይደሉም። እነዚህን አልጠግብ ባይ ሕሊና ቢስ ግለሰቦች የፌዴራል ፖሊስ ሕግ ፊት ለማቅረብ የሄደበት መንገድ የሚደነቅ ጠቋሚ ለህዝብና ለሀገር ያለውን ታማኝነት በአደባባይ ዳግም ያረጋገጠ ነው።

ኢትዮጵያ ባለፈው የመንግስት ስርአት ከሌላት መቀነት ፈታ፣ ከእለት ጉርሷ ቀንሳ ነገን የተሻለ ለማድረግ ለግዙፍ አገራዊ ፕሮጀክቶች ያወጣችው ጥሪት ጭምር እንዲህ ነው በማይባል ደረጃ ተዘርፏል። የመንግሥት ሃብትና ንብረት በተደራጁ ኃይሎች ምዝበራ ተፈፅሞበታል። ሜጋ ፕሮጀክቶች በታሰበላቸው ሰዓት ካለመጠናቀቃቸው ባሻገር ተጨማሪ ሃብት እንዲወጣባቸው የተደረገበት፣ ግልጽ ባልሆነ አሰራር እና በትውውቅ ፕሮጀክቶች ለሌብነት የተጋለጡበት አሰራር በስፋት ተስተውሏል።

ይህ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተንሰራፋ የሙስና ወንጀል ህዝቡን አስመርሮ በሀገሪቱ ለውጥ እንዲመጣ ገፊ ምክንያትም ሆኗል። ባለፉት አራት ዓመታትም የዘውግ ፖለቲካው ጡዘት፣አገር የገጠማት ጦርነትና የንጹሃን ዜጎች ግድያ የሙስናን ጉዳይ አለዘበው እንጂ አገርን ክፉኛ እያቆሰለ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም ይህ ክፉ የአገር ነቀርሳ መንግስታቸው እየተቸገረበት ከሚገኙ ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው መሆኑን በተለያዩ አጋጣሚዎች ለመላው ህዝብ አሳውቀዋል።

በቅርቡ በመዲናችን አዲስ አበባ የኮንዶሚኒየም ቤቶች እጣ አወጣጥ ላይ የተፈጠረው አሳፋሪ ድርጊትም አገርና ሕዝብ ምን ያህል በዚህ ችግር እየተበደሉ እንደሚገኙ ማሳያ ነው። እዚህ ላይ የፌዴራል ፖሊስ በብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ላይ የተፈጠረውን ዘረፋ እንዳጋለጠው ሁሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኮንዶሚኒየም ቤቶች እጣ አወጣጥ ላይ የተፈጠረውን ችግር ራሱ ደርሶበት ለሕዝብ ይፋ ማድረጉና ተጠርጣሪዎችንም በቁጥጥር አውሎ ርምጃ መውሰዱ የሚመሰገን ነው ።ሌብነትን ለመታገል ያለውን ቁርጠኝነት በተጨባጭ ያሳየበት ነው።

በርግጥ ኢትዮጵያ በሌብነት የገጠማት ፈተና መልከ ብዙ ነው። በክልሎችም ይሁን በፌዴራል ተቋማት ችግሩ ዛሬም ድረስ በስፋት ስለመኖሩ በርካታ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል። ሕዝብም ባገኘው ሁሉ አጋጣሚ ይህን ምሬት ሳይገልጽ አያልፍም። ሕዝቡን እየተፈታተነ ያለ ዋነኛ ነቀርሳ ነው። አገልግሎት ፈልገው ወደ ተለያዩ ተቋማት የሚያቀኑ ዜጎች በኃላፊነት አገልግሎት በደስታ መሸኘት ዛሬም ድረስ ፈተና የሆነባቸው ተቋማት ቁጥር ስፍር የላቸውም። እንኳን ተገልጋይ ቀርቶ ሰራተኞች ራሳቸው በተቋማቸው ብልሹ አሰራር ሲማረሩ መስማት ብርቅ አይደለም።

በሕዝብ ሃብትና ንብረት እንደ ግላቸው ጥሪት አድርገው ከህግም ከህሊናም ውጪ ተቋማትን የሚመሩና ተገልጋይን እንዲሁም ሰራተኞቻቸውን ጭምር የሚያማርሩ ሹማምንት የሉም ብሎ መንግስትም ቢሆን ደፍሮ መናገር አይችልም። መንግስት የተደላደለ ቤትና መኪና እንዲሁም ዳጎስ ያለ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ቸሯቸው አልጠግብ ባይ የተቋማት መሪዎች ዛሬም ሌላ ሃብትና ንብረት ለማጋበስ ሲቅበዘበዙ ማየት የተለመደ ነው።

ይህም ከዘውግ አስተሳሰብ ወጥታ የተረጋጋ ፖለቲካን እውን ለማድረግ ለምትታትር አንድ አገር ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ›› ነው። ሌቦች በመንግስትና በሕዝብ መካከል መተማመን እንዳይኖር እያመቻቹ ያሉት መንገድ በፖለቲካ ትኩሳቱ ላይ ቤንዚል እንደማርከፍከፍ ያህል ነው። ይህም አገርና ሕዝብ በምጣኔ ሃብት ረገድ ፈተና ውስጥ እንዲገቡ ከማድረጉ ባሻገር ቀን በቀን እየተመነደገ በመጣው የኑሮ ውድነት ትልቅ ሚና እንዲጫወት አድርጎታል።

ሙስና በኢትዮጵያ አብዝቶ መንሠራፋት እንደ ምክንያት ከሚጠቀሱ ጉዳዮች አንዱ የሲቪክ ማኅበራት በነፃነት መንቀሳቀስ አለመቻል፣ የፕሬስ ነፃነት መገደብ፣ የሕዝባዊ ተሣትፎ ማነስና የመንግሥት ለሕግጋት ተገዥ አለመሆን እንደሚገኙበት አንዳንድ ምሁራን ይናገራሉ። ይህንንም መንግስት መመልከት አለበት። ጥርስ የሌለው አንበሳ ተደርጎ የሚቆጠረው የጸረ-ሙስና ኮሚሽንን እንደ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንና ምርጫ ቦርድ ገለልተኛና ጠንካራ ሆኖ እንዲወጣ መንግስትም ተቋሙን የሚያጠናክርና አቅም እንዲኖረው የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት ረገድም ብዙ ርቀት መጓዝ ይኖርበታል።

ሙስና የሚፈጸምባቸው የወንጀል አይነቶች እየተራቀቁ እንደመምጣታቸው ወንጀሉን የመከላከልና የመመርመር ሥራው ተጣምሮ አቅሙ ባላቸው ብቁ ሠራተኞች ቢከናወን በየጊዜው ውጤታማ ስራዎችን ማከናወን እንደሚችልም ማሰብ ተገቢ ነው። ለዚህም የዜጎች የነቃ ተሳትፎ ወሳኝ ነው።

የሙስና ወንጀል በአገር ላይ እያስከተለ ያለውን ኪሳራ ለመከላከል የተደራጀና ንቃተ ህሊናው ከፍ ያለ ማኅብረሰብ ለመፍጠር እንዲሁም ጥፋተኞችን ተጠያቂ ለማድረግ፤ የሥነ-ምግባር እና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን፣ ፖሊስ እንዲሁም አቃቤ ሕግ በጥምረት ከመቼውም በላይ መስራት አለባቸው።ለዚህ የሚሆን አሰራር ማበጀትም ይኖርባቸዋል።

የፌዴራል ፖሊስ ሰሞኑን ያጋለጠው የሙስና ቅሌት የጭቃ ውስጥ እሾህ ሆነው መንግስትና ሕዝብን የሚመዘምዙ ተባዮችን ለመንቀል አበረታች ጅምር ቢሆንም የወረት መሆን የለበትም። ችግሩ በየቦታው አለና አበረታች ጅምሩ በህጋዊ ርምጃ ታጅቦ በስፋት ሊቀጥል ይገባል። ይህን ችግር ለመቅረፍ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ የተለያዩ ርምጃዎች ሲወሰዱ ነበር። ነገር ግን የአንድ ሰሞን መነጋገሪያ አጀንዳ ከመሆን የዘለሉ አይሆኑም። አሁንም መንግስት ከፍትህ ተቋማት ጋር በመሆን የጀመራቸውና በሂደት ላይ ያሉ ምርመራዎች እንደሚኖሩ ይታመናል። እነዚህን ጅምሮች አጠናክሮ በመቀጠል ከዳር አድርሶ ለሕዝብ ይፋ ለማድረግ የሰሞኑ ሞራል መቀዝቀዝ የለበትም።

ሙስና ለአንድ ሀገር እድገት እንቅፋት ከሆኑ ችግሮች መካከል የአንበሳውን ድርሻ ከመውሰድ በዘለለ ለአንድ አገረ መንግስት አለመረጋጋት ጉልህ ሚና አለው። መንግስት በዚህ ረገድ እየወሰደ ያለው እርምጃ መልካም ነው። ነገር ግን ያዝ ለቀቅ የሚደረግ ከሆነ እርምጃው በራሱ ለሌላ ፖለቲካዊ ትርጉም የመጋለጥ እድል አለው። ስለዚህ መንግስት በሌብነት ላይ የመዘዘውን ሰይፍ በየቦታው የተዘረጋውን የሌብነት ሰንሰለት እስኪበጥስ ድረስ ወደ ሰገባው ሊመልሰው አይገባም።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## “ፉትቦል ... !?”

መቼም አሸባሪው ሕወሓት ነፍሱ አይማርም ባለፉት አራት ዓመታት ጊዜዬን ፣ አእምሮዬንና ጉልበቴን እሱ ላይ እንዳፈስ አስገድዶኛል ። ነገሬን ሁሉ ከእጄ አስጥሎ ስለ እርሱ ብቻ እንድጽፍ አስገድዶኛል ። አሁንም እግዜሩ ይይለትና ነፍሱም አይማርና በዚህ የተነሳ ኦፊሴላዊ ባይሆንም አንጋፋው “አዲስ ዘመን”/የኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ “የሕወሓት ጉዳዮች ቋሚና ልዩ ዘጋቢ !?”አድርጎኝ አርፏል ። በዚህ አጋጣሚ እነ በዓሉ ግርማ ፣ ብርሀኑ ዘሪሁን ሙሉጌታ ሉሌና ሌሎች ጉምቱ ጋዜጠኞችና ጸሐፍት በተሰናዘሩበት “አዲስ ዘመን” ለመጻፍ እድሉን በማግኘቴ ከፍ ያለ ክብር ይሰማኛል ።

አብዝቼ ስለ አሸባሪው ሕወሓት መጻፌ ደግሞ ያናድደኛል። ያስቆጨኛል ። ሆኖም ለሀገሬና ለሕዝቤ እንዲሁም ለውጡ ከእነ ውስንነቶቹና ድክመቶቹም ቢሆንም ዳር እንዲደርስ የከፈልሁት ዋጋ ስለሆነ እጽናናለሁ ። ወደ ተነሳሁበት ሀሳብ ስመለስ ስለ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ፣ ስለ ስነ ጽሑፍ ፣ ኪነ ጥበብ ፣ ኪነ ሕንጻ ፣ ስዕል፣ ሙዚቃ ፣ ስፖርት ፣ ወቅታዊ ዓለማቀፍ ጉዳይ ፣ ወዘተረፈ. ግድ እንደማይሰጠኝ በተለይ አሸባሪው ሕወሓት ላይ ማተኮሬ ሌላ ጉዳይ ላይ እንዳላንሰላስልና እንዳልጽፍ ጠምዶ ይዞኝ ነበር ።

ዛሬ በስንት ትግል ጥማዱን ፈትቼ ለ2ኛ ጊዜ ስለወቅታዊ ዓለም አቀፍ ጉዳይ ለዛውም ስለ አሸባሪው ሕወሓት ምንም ሳላነሳ ይቺን መጣጥፍ ጫጭሬያለሁ ። ለራሴ እንኳን ለዚህ አበቃህ ብል መቼም አይበዛብኝም ። በባሕሪዬ ጨለምተኛም ሚርተኛም አይደለሁም ። ሰብዕናዬንና ስሜቴን አውልቄ ወደ ጋዜጠኝነት ስመለስ ግን እንደ ሰው ልጅ ለማሰብ እሞክራለሁ። ተስፋውንም ስጋቱንም እጋራለሁ ።

ሩሲያ ዩክሬንን መውረሯን ተከትሎ የተቀሰቀሰው ዳግማዊ ቀዝቃዛ ጦርነት ምን አልባት በኒውክሌርና በሳይበር ለታገዘ 3ኛው የዓለም ጦርነት ይዳርገን ይሆን በሚል ስጋቴን በዚሁ ጋዜጣ አጋርቼ ነበር ። ዛሬ ደግሞ “ፉትቦል “ ስለተሰኘው የአሜሪካ የኒውክሌር ጦር ማዘዣ ቦርሳ፤መረጃ አቀብላለሁ ። እንደ ፈጣሪ ፈቃድ ደግሞ ስለ ሩሲያው የኒውክሌር ጦር ማዘዣ “ቼጌት”አስከትዬ እጽፋለሁ።

የአሜሪካ የቀድሞ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ከቀደሚቻቸውም ከተከተሏቸውም ለየት ያለ ልምድ ነበራቸው። ሰርክ ጥዋት ቢሮ ሲገቡ መጀመሪያ የሚያደርጉት በጠረጴዛቸው የተቀመጠውን የዓለም ሉል/Globe/ ያሽከረክሩና ሶቭየት ኅብረት ላይ ሲደርስ ያቆሙትና የጥሞና ጊዜ ይወስዱና ። የኒውክሌር ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ይጸልያሉ።

በአንጻሩ ፕሬዚዳንት ጆን ኤፍ ኬኔዲ ደግሞ የሶቪየት ኅብረት የኒውክሌር ሚሳየል ኩባን ከአሜሪካ ጥቃት ለመከላከል ተጠምዶ ስለነበር ያለ ሞስኮ እውቅና ጥቃት ሊፈጸምብን ስለሚችል ፈጣን የአጸፋ ምላሽ? የምንሰጥበት አሠራር ያስፈልጋል በሚል የዛሬው የፉት ቦል አጠቃቀም ተግባራዊ ሊደረግ ችሏል ። ለመሆኑ ይህ ከአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች አጠገብ የማይለየው የኒውክሌር ጦር መሣሪያ ማዘዣ ቦርሳ”ፉትቦል” እንዴት ያለ ነው !?

የኒውክሌር ጦር መሣሪያን ለማዘዝ የሚያስችል መሣሪያን አልያም ቁልፍን ለመያዝ ተብሎ በልዩ ሁኔታ የተሠራ ሳምሶናይት ወይም ቦርሳ የኒውክሌር ሳምሶናይት ወይም ቦርሳ ይሰኛል ። መሪዎች ከሀገር ሲወጡ ፤ እንደ አሜሪካ ባሉ ሀገራት ደግሞ ከአንዱ ግዛት ወደ ሌላው ሲንቀሳቀሱ ከኋላ ወታደራዊ መለዮ በለበሰ የጸጥታ ሰው ተይዞ ሲከተል የሚታየው የኒውክሌር ጦር መሣሪያ ማዘዣን የያዘ ቦርሳ ነው። ሆኖም የኒውክሌር ጦር መሣሪያ የታጠቁ ሀገራት ሁሉ እንደ አሜሪካና ራሽያ የኒውክሌር ማዘዣቸውን በሳምሶናይት ወይም በቦርሳ ይዘው ይዞራሉ ማለት አይደለም።

ፈረንሳይ የኒውክሌር የጦር መሳሪያ ከታጠቁ ሀገራት አንዷ ብትሆንም ኦፊሴላዊ የኒውክሌር ማዘዣ ቦርሳ የላትም። ይሁንና ከፈረንሳይ ፕሬዚዳንት አጠገብ የማይለይ ሳምሶናይት አለ ። ዳሩ ግን የኒውክሌር ማዘዣ መሣሪያ ስለመያዙ እርግጠኛ የሆነ የለም ። ሕንድ የኒውክሌር ጦር መሣሪያ ብትታጠቅም ፤ ከጠቅላይ ሚኒስትሯ አጠገብ የማይለይና አብሮ ዓለምን የሚዞር የኒውክሌር ቦርሳ ወይም ሳምሶናይት የለም ።

እንዲያውም የሕንድ የኒውክሌር ጦር መሣሪያ እንደ ሌሎች ሀገራት በሀገሪቱ መሪ ሳይሆን የሚታዘዘው ለዚሁ የተለየ ተልዕኮ በተቋቋመው የ”ኒውክሌር ማዘዣ ባለስልጣን፤”አማካኝነት ነው ። ባላንጣዋና ጎረቤቷ ፓኪስታን ግን ከመሪዋ አጠገብ የማይለይ የኒውክሌር የጦር መሣሪያ ማዘዣ የያዘ ሳምሶናይት አላት ። በሕንድ የኒውክሌር ጦር መሣሪያ ማዘዣው በመሪው ብቻ ሳይሆን ለዚሁ በተቋቋመ ባለስልጣን መመራቱ ከግብታዊና ስሜታዊ ውሳኔዎች ይታደጋል ።

የአሜሪካው የኒውክሌር ጦር መሣሪያ ማዘዣን የሚይዘው ቦርሳ “አቶሚክ ፉትቦል” ወይም “ፉትቦል” በመባል ቢታወቅም ፤ “የአደጋ ጊዜ ቦርሳ” ፣ “ቁልፉ” እና “ጥቁሩ ሳጥን” የሚሉ ቅጽሎች አሉት ። የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በዋሽንግተን በኋይታወስ ከሆኑ የከፍተኛ ወታደራዊ ዘመቻዎች በሚመሩበት “ሲቹየሽን ሩም” በመባል በሚታወቀው ክፍል ከካቢኔያቸውና ከአማካሪዎቻቸው ጋር ሆነው ነው ። ከነጩ ቤተ መንግሥት ውጭ ከሆኑ ግን በየትኛውም ቦታና ምንጊዜም ከአጠገባቸው የማይጠፋውን “ፉትቦል”ን ተጠቅመው የኒውክሌር ጥቃትን ያዛሉ ።

“ፉትቦል”ተንቀሳቃሽ የኒውክሌር ጦር መሣሪያ ማዘዣ ማዕከል ነው ። የቀድሞው የኋይታወስ ወታደራዊ ቢሮ ዳይሬክተር ቢል ጉሌ ፤” በፉትቦል”ውስጥ አራት ሁነኛ ነገሮች ይገኛሉ ይለናል ። የመጀመሪያው ጥቁሩ መጽሐፍ የሚባል ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ በጥብቅ ሚስጥር የሚጠበቁ ቦታዎችን የሰነደ መጽሐፍ ፤ ሶስተኛው “የማኒላ ማህደር” ሲሆን የአደጋ ጊዜ መልዕክት ማሰራጫውን አጠቃቀም የሚያብራራ ነው ። አራተኛው ደግሞ የማረጋገጫ ምስጢር የያዘ ካርድ ነው ። ጥቁሩ መጽሐፍ በጥቁርና በቀይ የተተየቡ 75 ገጾችን ሲይዝ ፤ በጥብቅ ሚስጥር የሚጠበቁ ቦታዎችን የሰነደው መጽሐፍም እንደ ጥቁሩ መጽሐፍ ተቀራራቢ ገጽ ያለውና ጥቁር ሲሆን እንደ ነውክሌር ጥቃት ባለ አደጋ ጊዜ ፕሬዚዳንቱ በሀገሪቱ የት የት ሊጠለሉ እንደሚችሉ የሚያመለክት እጅግ ጥብቅ መረጃ ነው ።

በ2005 ዓም በዋሽንግተን ፖስት ለንባብ በበቃ መጣጥፍ ፤”ፉትቦል”የኒውክሌር ጦር መሣሪያ ማስተኮሻ ምስጢራዊ ቁልፍ የያዘ መሆኑን ያትታል። ክብደቱ 20 ኪ.ግ ሲመዝን ፣ የኮሙኒኬሽን አንቴናም አለው። ይህ “ፉትቦል” የኮሙኒኬሽን መሣሪያም እንደያዘ ያመለክታል። ፕሬዚዳንቱ በተንቀሳቀሱበት ሁሉ ፉትቦሉን ይዞ የሚከተለው ወታደራዊ የደንብ ልብስ ከላይ እስከታች የገደገደው የጸጥታ ሰው ፎቶ ሳይቀር በዚሁ የኒውክሌር መልዕክተኛ ቦርሳ ይገኛል ሲል ዋሽንግተን ፖስት በአግራሞት ይገልጻል ።

የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ የሆኑት ፕሬዚዳንቱ የኒውክሌር የጦር መሣሪያን ለመጠቀም ከወሰኑ “ፉትቦሉን” ይዞ እንደ ጥላ የሚከተለው ወታደር ፕሬዚዳንቱን ወደ ዘዋራ ቦታ ይወስድና ይከፍትላቸዋል ። ወዲያው ወደ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦሩ ሹም ማዘዣ የማስጠንቀቂያ ምልክት ይተላለፋል ። በማስከተል ፕሬዚዳንቱ ከኤታማዦር ሹሙና ከመከላከያ ሚኒስትሩ ጋር የጥቃት ኢላማዎችን ይለያሉ። ከዚያ እንደ አስገዳጅ ሁኔታው አንድ ወይም በርካታ አህጉር አቋራጭ የባሊስቲክ ሚሳየል ሊተኮስ ይችላል። ይህ ውሳኔ የቀድሞው አንድ ወጥ የተቀናጀ የዘመቻ ዕቅድ ወይም የአሁኑ ኦፕላን 8010 ወይም OPLAN/OPerational pLAN/ አካል ነው ።ሚሳየሉ ከመተኮሱ በፊት ፕሬዚዳንቱ “ብስኩት” በመባል የሚታወቀውን የፕላስቲክ ካርድ እንደ ይለፍ በመጠቀም ያረጋግጣሉ ። የመከላከያ ሚኒስትሩም ትዕዛዙ በእርግጥ በፕሬዚዳንቱ የተላለፈ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ በተዋረድ የመጨረሻ ማረጋገጫ ለምድብተኛ ተኳሽ ትዕዛዝ ይሰጣሉ ። ሆኖም እያንዳንዱ ውሳኔ በጥልቅ ይመረመራል። ይረጋገጣል ። ይህ ማለት የፕሬዚዳንቱ ስልጣን ገደብ የለሽ ነው ማለት አይደለም።

የአሜሪካ ሕግ ጥቃቱ ሕጋዊ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል። ፕሬዚዳንቱ የጦርነትን ሕግ ተላልፎ ትዕዛዝ የሚሰጥ ከሆነ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙም ሆነ በተዋረድ ያሉ ባለ አራት ኮከብ ጀነራሎች ወይም አድሚራሎች ውሳኔውን ያለመቀበል መብት አላቸው። ጄነራል ጆን ሀይተንን ጨምሮ በርካታ ወታደራዊ አዛዦች ሕገ ወጥ የኒውክሌር ጥቃት ትዕዛዝን እንደማይቀበሉ በኮንግረሱ ፊት ሳይቀር ቀርበው መተማመኛ ሰጥተዋል። ጥቃቱ ከመፈጸሙ የሕግ ባለሙያዎችም ማረጋገጫ እንዲሰጡ ይደረጋል ።

በአጠቃላይ ሶስት የኒውክሌር “ፉትቦል”ሲኖር ፤ ሁለቱ በፕሬዚዳንቱና በምክትል ፕሬዚዳንቱ እጅ ሲገኙ ፤ ሶስተኛው ደግሞ በቋሚነት በኋይታወስ ቤተ መንግሥት ይቀመጣል ። ፕሬዚዳንቱ በተለያዩ ምክንያቶች ኃላፊነታቸውን መወጣት የማይችሉ ከሆነ ምክትሉ በእግራቸው ይተካሉ ። ይህ አሠራር የተጀመረው በጂሚ ካርተር አስተዳደር ነው ። ምን ጊዜም ቢሆን የ”ፉትቦል”ሚስጥራዊ ካርድ ከአንዱ ፕሬዚዳንት ወደ ተተኪው የሚተላለፈው በቂ ገለጻና ማብራሪያ ከተሰጠ በኋላ ነው ።

ተሰናባቹ ፕሬዚዳንት ተተኪውን በቤተ መንግሥት ከተቀበሉ በኋላ መልካም የሥራ ዘመን እንዲሆንላቸው በመመኘት “ፉትቦል”ንም ያስረክቡታል። አዲሱ ፕሬዚዳንትም በዓለ ሲመቱን ካከናወኑና ቃለ መሐላ ከፈጸሙ በኋላ የኒውክሌር ጦር መሣሪያ ማዘዣን ሚስጥራዊ ቁልፍ ይረከባሉ ። በዘመነ ፕሬዚዳንት ትራምፕ የሆነው ግን እንግዳና ያልተጠበቀ ነበር ። በአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች ታሪክ ብዙ ባልተለመደ ሁኔታ አፈንጋጩና አወዛጋቢው ተሰናባች ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ግን የምርጫ ውጤቱን አልቀበልም በማለት ፤ ተመራጩን ፕሬዚዳንት ጆ ባይደንን በኋይታወስ ካለመቀበላቸው ባሻገር በበዓለ ሲመቱም አልተገኙም ።

ፉትቦሉንም ሳያስረክቡ ወደ ፍሎሪዳ በመሔዳቸው ወዲያው እንዳይሠራ ከመደረጉ ባሻገር ከፕሬዚዳንቱ ጋር የነበረው አቃቤ ፉትቦል ወደ ኋይታወስ በአስቸኳይ ይዞ እንዲመለስ ታዟል ። የኒውክሌር “ፉትቦል”ዘፍጥረት ከፕሬዚዳንት አይዘንሀወር የሚነሳ ሲሆን ፤ ከፍ ብሎ የተመለከተውን አሠራር መከተል የተጀመረው ግን ከኩባው የሚሳይል ቀውስ በኋላ በጆን ኤፍ ኬኔዲ የስልጣን ዘመን ነው።

“ፉትቦል”የሚለው መጠሪያ ስረወ-ቃል የመጣው “ኳስ መለጋት/Dropkick”ከሚለው ልዩ መጠሪያው ሲሆን፤ በተወዳጁ የአሜሪካ ፉትቦል ደግሞ ኳስን መለጋት የጨዋታው አካል ስለሆነ”ፉትቦል”ሊባል ችሏል ይለናል የአሜሪካው የዜና አገልግሎት አሶሼትድ ፕሬስ/ኤፒ/ ። ከሰው መርጦ ለሹመት ፣ ከእንጨት መርጦ ለታቦት ፤ እንዲሉ በፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተርና ሮናልድ ሬገን የአስተዳደር ዘመን “ፉትቦሉን” በኃላፊነት ይዞ ይከተላቸው የነበረው ኮሎኔል ጆን ክሊኔ ነበር ።

በነገራችን ይህ ኃላፊነት በዙር ለምድር ፣ ለባሕርና ለአየር ኃይሉና ለሌሎች የመከላከያና የጸጥታ መሥሪያ ቤቶች ሲሰጥ፤ እያንዳንዱ ወታደራዊ ክፍል ተራው ሲደርስ እጩውን በጥንቃቄ ይለይና ለአሜሪካ የስለላ ድርጅት/ ሲአይኤ/ያቀርባል። የቀደመም የአሁንም ማንነቱ በደንብ ተብጠርጥሮ ተፈትሾ መስፈርቱን ሲያሟላ ፉት ቦሉን ለመያዝ ብቁ ይሆናል።

እዚህ ላይ አንድ አስገራሚ ገጠመኝ ላንሳ ፤ የፕሬዚዳንቱ ትዕዛዝ የሚረጋገጥበት “ብስኩት” በመባል የሚታወቀው የፕላስቲክ ካርድ መቼም ቢሆን ከፕሬዚዳንቱ እጅ ወይም ኪስ አይጠፋም ። በ1981 ዓ.ም በፕሬዚዳንት ሮናልድ ላይ የግድያ ሙከራ ተደርጎ ፤ የድንገተኛ ክፍል ሐኪሞች ሕይወታቸውን ለመታደግ እንዲያፈጥናቸው ልብሳቸውን በመቀስ ቀደው እርዳታ ያደርጉላቸዋል ።

የፕሬዚዳንቱ ጉዳት ለክፉ እንደማይሰጥ ሲረጋገጥና ሁኔታዎች ሲረጋጉ ፤ የደህንነት ሰዎችም ወደ ቀልባቸው ሲመለሱ “ብስኩቱ” ሲፈለግ ይጠፋል ። ወዲያው ሁሉም ይደናገጥና በየፊናው ፍለጋ ይገባል ። ከብዙ ድካም በኋላ ባልተገመተ ቦታ ላይ ማለትም በፕሬዚዳንቱ ጫማ ውስጥ ተወሽቆ ይገኛል ። እንዴት በፕሬዚዳንቱ ጫማ ውስጥ ሊገባ እንደቻለ ዛሬም መልስ አልተገኘለትም ።

አብጠልጣይ የሆነው ሚዲያው በኋላ ላይ ፕሬዚዳንት ሬጋን ሚስጥራዊ ቁልፉን ለካ በካልሲያቸው ውስጥ ነበር የሚይዙት በማለት ተሳለቀ ። ፉትቦሉና ፕሬዚዳንቶች በተደጋጋሚ እየተለያዩ ጭንቅ ጥብ የተሆነባቸው ሰዓታትም ነበሩ ይለናል ኤፒ ። በፕሬዚዳንት ሬጋን ላይ የግድያ ሙከራ የተደረገ ጊዜ ፤ ፕሬዚዳንት ሪቻርድ ኒክሰን በ1973 ዓም የሶቪየት ኅብረቱን መሪ ሊዎኒድ ብሬዥኔቭ በተቀበሉ ዕለት፤ ፕሬዚዳንት ጌራልድ ፎርድ ፣ ጂሚ ካርተር ፣ ጆርጅ ኤች ደብሊው ቡሽና ቢል ክሊንተንም በተለያዩ አጋጣሚዎች ከፉትቦል ተለይተው ያውቃሉ ።

የኒውክሌር ፉትቦሉን ሁል ጊዜ ከፕሬዚዳንቱ በቅርብ እርቀት መሆን ስላለበት ፤ የያዙት መኮንኖች ምስል በጋዜጠኞች ካሜራ አደባባይ መዋሉ የተለመደ ነው ። አወዛጋቢው ፕሬዚዳንት ትራምፕ ያደረጉት ግን ከዚህ ወጣ ያለ ነበር ። ፉትቦሉን ከያዘው መኮንን ጋር ቆሞ ፎቶ ይነሳና ስሙን ተገልጦ በፌስቡክ ይለጠፋል ።

ይህ የሆነው የወቅቱ የጃፓን ጠቅላይ ሚኒስትር ሺንዞ አቤ አሜሪካንን እየጎበኙ ፤ ሰሜን ኮሪያ የረጅም ርቀት ተወንጫፊ ሚሳየል ሙከራ ካደረገችበት ሰዓት ጋር ሁኔታዎች ስለተገጣጠሙ እና አንድምታውም ከጸረ የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ፉክክር መርህ ጋር ስለሚጻረር፤ የአሜሪካ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ያልተለመደውን ሁኔታ በማውገዝ ድርጊቱም ሕገ ወጥ መሆኑን ፤ ፉትቦሉን የያዘው መኮንን ፎቶ መነሳቱ ስህተት እንደነበር ገልጸዋል ። ፕሬዚዳንት ትራምፕ በሕዳር 2017 ዓ.ም ቻይና ለኦፊሴላዊ ጉብኝት ባቀኑበት ወቅት ከሀገሪቱ መሪ ዢ ዢንፒግ ጋር ለመነጋገር ወደ ተዘጋጀ የመሰብሰቢያ አዳራሽ እየገቡ ሳለ

የፕሬዚዳንት ትራምፕ አጃቢዎችና ፉትቦሉን የያዘው መኮንን በአንድ በኩል ፤ የፕሬዚዳንት ዥንፒንግ አጃቢዎች በሌላ በኩል እኔ ልቅደም እኔ እያሉ ግብግብ ሲገጥሙ ፉትቦሉ አደጋ ላይ ወድቆ እንደነበር በወቅቱ በስፍራው የነበረው የፖለቲካዊ ጉዳዮች ዘጋቢ ጆናታን ስዋን እማኝነቱን ሰጥቷል ። ሆኖም ለተፈጠረው እንግዳ ነገርና ስህተት የቻይና የጸጥታ ኃላፊዎች ይቅርታ ጠይቀዋል ።

ጥር 6 ቀን ፣ 2021 ዓ.ም የትራምፕ ደጋፊዎች የምርጫውን የኤሌክቶራል ኮሌጅ ድምጽ ውጤት ለማጽደቅ በወቅቱ ምክትል ፕሬዚዳንት ማይክ ፔንስ ሰብሳቢነት ሴኔቱ በካፒቶል ሒል ተሰብስቦ እያለ ደርምሰው በገቡበት ወቅት ምክትል ፕሬዚዳንቱ ፣ ቤተሰቦቻቸውና ሴናተሮች ለደህንነታቸው ወደ ማያሰጋ ምስጢራዊ ቦታ በመውሰድ ከጥቃት ማትረፍ ቢቻልም ፤ ፉት ቦል ግን በሁከተኞች እጅ ከመውደቅ ለትንሽ መትረፉ ሌላው መነጋገሪያ ነበር ።

ከፍተኛ ሚስጥራዊ መረጃዎች በተለይ የኒውክሌር ጥቃት ሊሰነዘርባቸው የሚችሉ ኢላማ ዝርዝሮች ፤ በአሜሪካ ጥቃቱ ቢሰነዘር ፕሬዚዳንቱ የሚጠለሉባቸው ምስጢራዊ ቦታዎች፤ ባልተገቡ አካላት እጅ ወድቀው የሀገሪቱን ደህንነትና ጸጥታ አደጋ ላይ ጥለውት ነበር በሚል ድንጋጤ ፈጥሮ አልፏል ። የትራምፕ ደጋፊዎች የአሜሪካ ልሒቃን እንደ ዴሞክራሲ ቤተ መቅደስ የሚያዩትን ካፒቶል ሒልን በሀይል ሰብረው ገብተው በነበረበት ወቅት ምክትል ፕሬዚዳንቱና ፉትቦሉ ተጠልለው በነበሩበት ክፍል በ30 ሜትር እርቀት ተቃርበው ስለነበር መሠል ተጋላጭነት እንዳይኖር የመከላከያ ሚኒስቴር ዋና ተቆጣጣሪ ምርመራ ጀምሯል ።

ኋይታወስና ፔንታጎን እንደዚህ ያለ መሰል ቀውስ ቢያጋጥም ፤ ፉት ቦሉ እንዳይሰረቅና እንዳይጠፋ ደህንነቱን ማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አለመዘርጋታቸውን እያጣራ ነው ። የምርመራውና የማጣራቱ ግኝት በያዝነው የሐምሌ ወር ይፋ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል ። የኮንግረስ አባላቱ ስቴፈን ሊንችና ጂም ኮፐር ፤ ፉትቦሉን አስመልክቶ ዋና ተቆጣጣሪው ምርመራና ግምገማ መጀመሩ ትክክለኛ ውሳኔ መሆኑን ገልጸው በካፒቶል ሒል ላይ የተፈጸመው ጥቃት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓታችን ላይ የተፈጸመ ጥቃት ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የሀገራችንን ደህንነት ለአደጋ ያጋለጠ እኩይ ተግባር ነው ብለዋል ።

በጥቃቱ ዕለት ምክትል ፕሬዚዳንት ማይክና ፉትቦሉን የያዘው ረዳታቸው የተደበቁበት ቦታ ከአመጻኞች በቅርብ ርቀት ላይ ስለነበሩ ፉትቦሉ በአመጻኞች እጅ ሊወድቅ ሰከንዶች ቀርተውት እንደነበር ፔንታጎን እራሱ መረጃው እንዳልነበረው የኮንግረስ አባላቱ ከሲኤንኤን ጋር በነበራቸው ቃለ መጠይቅ አስታውቀዋል ።

ሆኖም ፉት ቦሉ ላይ አደጋ ቢደቀን እንዴት መከላከል እንደሚቻል በግልጽ የተቀመጠ ቅደም ተከተልና የራሱ የአፈጻጸም ሒደት እንዳለው ብናውቅም ደህንነቱን የሚያረጋግጡ አሠራሮችን በየጊዜው መፈተሽና ማሻሻል ግን ግድ ይላል ብለዋል።

ሲኤንኤን ያነጋገራቸው ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዥ ግን ፉት ቦሉን የያዘው መኮንን እንዴት ከአደጋ መከላከል እንዳለበት ጠንቅቆ ያውቃል ካለ በኋላ በማስከተል የከፋ ነገር ቢከሰት ደግሞ ወዲያው እንዳይሠራ በማድረግ መቆጣጠር ይቻላል በማለት ስጋቱን ያቃልሉታል ። ፈጣሪ ዓለማችንን ከኒውክሌር ጦርነት ይጠብቅ ! አሜን ።

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የኢንኩቤሽን ማዕከላት የቴክኖሎጂው ዘርፍ የእድገት መሰረቶች

**አንተነህ ቸሬ**

ከአስር ዓመቱ ሀገራዊ የልማት እቅድ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች (Strategic Pillars) መካከል አንዱ የቴክኖሎጂ አቅም እና ዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት ነው። ይህን ለማሳካት ደግሞ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዘርፉን ውጤታማነት ማሳደግ ወሳኝ ግብዓት እንደሆነ ይታወቃል።

የዘርፉን ውጤታማነት ለማጎልበት ከሚተገበሩ አቅጣጫዎች መካከል ጀማሪ ስራ ፈጣሪዎች ሃሳባቸውን ወደ ቢዝነስ ተግባራት የሚያሸጋግሩባቸው የኢንኩቤሽን ማዕከላት ይጠቀሳሉ። የቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከላት፣ የተለያዩ ድጋፎች ተደርገውላቸው የፈጠራ ሃሳቦችን ወደ ቢዝነስ ማሳደግ የሚያስችል ከባቢ የሚፈጥሩና ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና ኢንዱስትሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ወጣቶች ልምድ እንዲያገኙ የሚያስችሉ ማዕከላት ናቸው።

እነዚህ ማዕከላት በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የተቋቋሙ ሲሆን፣ በየክልሎቹ ከሚገነቡ የቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከላት በተጨማሪ በትምህርት ተቋማት፣ በሲቪል ማህበራት እና በመንግስት ድርጅቶች ውስጥ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ባህልን በተጨባጭ ለማሳደግ የሚረዱ አዳዲስ አሰራሮችን ለመዘርጋት እና የኢኖቬሽን ስነ-ምህዳሩን ለማሻሻል የሚያስችሉ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ።

በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የኢኖቬሽን ልማትና ምርምር ዘርፍ ዳይሬክተር አቶ ሰላምይሁን አደፍርስ፣ የቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከላት ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽንን መሰረት ያደረጉ ጀማሪ ስራ ፈጣሪዎች (Startup Businesses) ሃሳባቸውን ወደ ቢዝነስ እና ሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ወደ አላቸው ተግባራት የሚያሸጋግሩባቸው ማዕከላት ወይም ተቋማት እንደሆኑ ያስረዳሉ።

የቴክኖሎጂ ጀማሪ ቢዝነሶች (Technology Startup Businesses) ሲባሉ በመሰረታዊነት አዲስ ወይም የነበሩ ኢንተርፕራይዞች ሆነው፤ ሳይንስ (ምርምር)፣ ቴክኖሎጂ ወይም ቢዝነስ ላይ የተመሰረተ አዳዲስ የፈጠራ ስራዎች ያላቸው፤ በአንድ ሰው ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች ስብስብ የሚፈጠሩ የቢዝነስ ዓይነቶች ሲሆኑ፤ እምቅ የማደግ አቅም እና ይህንንም የማሳካት ቁርጠኙነቱና ብቃቱ ያላቸው፤ ወሳኝ የመወዳደር አቅማቸው ፈጠራ የሆነና ቴክኖሎጂን በቢዝነስ ሞዴላቸው ውስጥ የሚጠቀሙ ናቸው።

ይሁን እንጂ እነዚህ የቢዝነስ ስራዎች በአብዛኛው በቀላሉ ሊጠፉ የሚችሉ (Volatile) እና በከፍተኛ እርግጠኛነት በሌለው (Uncertain) ሁኔታ የተከበቡ ናቸው። ስለሆነም በተለየ ሁኔታ በመንግስትም ሆነ በግል የሚፈጠሩ የሳይንስ (ምርምር)፣ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከላት ዋናው ስራቸው እንዲህ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን መሰረት ያደረጉ ጀማሪ ቢዝነሶች እንዳይጠፉ ማድረግ እና መሰናክሎችን በማሻገር ቀጣይነት አደ አለውና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳቸው ከፍተኛ ወደሆኑ ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረጉ የግል የቢዝነስ ተቋማት ማሸጋገር ነው። ከግል ዘርፉ ባሻገር በመንግሥት የሚሰሩ መሰል ተቋማትም ለታዳጊ አገራት እድገት ቁልፍ ሚና እንደሚኖራቸው በዘላቂ የልማት ግቦች (Sustainable Development Goals) ላይ በግልጽ ተመላክቷል።

ማዕከላቱ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል ሃሳብ የሚመነጭበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤ ሃሳቦች የሚሞከሩባቸው የመስሪያ ቦታዎች፣ ላቦራቶሪዎች፣ መሰረተ ልማቶችና የቁሳቁስ አገልግሎት ማቅረብ፤ የፈጠራ ውድድሮችንና ሽልማቶችን ማከናወን እንዲሁም ከተለያዩ የኢኖቬሽን ስነ ምህዳር አካላት፣ ማለትም ከምርምር ተቋማት፣ ከባለሀብቶች፣ ከፋይናንስ ተቋማትና ከማኅበራት ጋር ግንኙነት የሚደረግበት ማዕከል ሆኖ ማገልገል የሚሉት ይጠቀሳሉ።

በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ከ15 በላይ የቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከላት እንደሚገኙ አቶ ሰላምይሁን ይገልፃሉ። ከእነዚህም መካከል በኦሮሚያ ክልል (በአዳማና ጅማ)፣ በአማራ ክልል (በባህር ዳርና ጎንደር)፣ በሶማሌ ክልል፣ በአዲስ አበባ ከተማና በሌሎች አካባቢዎች የሚገኙ ማዕከላት ተጠቃሽ ናቸው። ማዕከላቱ በዋናነት የቴክኖሎጂ፣ ኢኖቬሽንና ሳይንስ ባህል እንዲጎለብት ማድረግን ብቻ ታሳቢ ተደርገው የተሰሩ ናቸው። በቀጣይ ጊዜያት አካታች የሆኑ የቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከላትን ለማጎልበት የሚያስችሉ ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል።

በሌላ በኩል ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የተቋቋሙ የቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከላትም አሉ። ለአብነት ያህል በኮሪያ ዓለም አቀፍ ትብብር ኤጀንሲ (ኮይካ) በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ (Information Communication Technology Park) ውስጥ በሁለት ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ እየተገነባ የሚገኘው « Kinobiz Center» እና ኦሬንጅ ዲጅታል ማዕከል (Orange Digital Center) ይጠቀሳሉ።

በመንግሥት ከተቋቋሙ የኢንኩቤሽን ማዕከላት በተጨማሪ የግል ኢንኩቤሽን ማዕከላትን ማስፋፋትም ትኩረት የሚሰጠው ተግባር እንደሆነ የሚናገሩት አቶ ሰላምይሁን፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርም የፖሊሲ ማሻሻያዎችን በማድረግ ለግል የኢንኩቤሽን ማዕከላት መስፋፋት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ ይናገራሉ። በግል ዘርፉ ከሚጠቀሱ የቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከላት መካከል «አይስ አዲስ» (Ice Addis)፣ «ብሉ ሙን» (Blue Moon) እና «1888EC» የሚባሉት ይገኙበታል። ከእነዚህ የግል ኢንኩቤሽን ማዕከላት ጋር በተደረገ ትብብር ብዙ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ወጣቶችንና ታዳጊዎችን ማገዝ ተችሏል።

የኢንኩቤሽን ማዕከላቱ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸው ሰዎች ስራዎቻቸውን ወደ ተግባር እንዲቀይሩና ከስራዎቻቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ሚናቸው የጎላ መሆኑን በመጥቀስ፣ የማዕከላቱ መቋቋም አበረታች ውጤቶችን ማስገኘቱንም አቶ ሰላምይሁን ያስረዳሉ።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የማዕከላቱ መቋቋም ጀማሪ ቢዝነሶች በሃገሪቱ እየተበራከቱ እንዲመጡ በር ከፍቷል። በተለያዩ መንገዶች በእነዚህ ማዕከላት ተደግፈው ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን ማሸነፍ የቻሉ ጀማሪ ቢዝነሶች መፈጠር ጀምረዋል። ከ500 በላይ እምቅ አቅም ያላቸው ስታርትአፕ ቢዝነሶችንና እስከ 38 ሚሊዮን ብር የሚደርስ ሀብት መፍጠር ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪም የማዕከላቱ መቋቋም የኢኖቬሽን ባህል ግንዛቤና አስፈላጊነት እንዲያድግ እድል ፈጥሯል።

በኢኖቬሽን ስነ-ምህዳር ውስጥ ቁልፍ ሚና ካላቸው አካላት ውስጥ የሚጠቀሱት እነዚህ የኢንኩቤሽን ማዕከላት፣ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ሰዎች ወደ ምርትና አገልግሎት በማምጣት ረገድ በጎ አስተዋፅኦዎችን የሚያበረክቱ መሆናቸውን በመግለጽ፣ መንግሥት ለማዕከላቱ ልዩ ልዩ ድጋፎችንና ክትትሎችን ያደርጋል ይላሉ።

በዚህ ረገድ ለማዕከላቱ ስለሚደረገው ድጋፍና ክትትል አቶ ሰላምይሁን ሲያብራሩ «መንግሥት ከማዕከላቱ ዲዛይን ጀምሮ በማቴሪያል እስከማደራጀት የዘለቀ ድጋፍና የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል። በመዋቅር፣ በህግና በፖሊሲ እንዲደገፉ የማድረግ፤ የተለያዩ ስልጠናዎችና ተያያዥ ድጋፎችን የማቅረብ፤ ለችግሮቻቸው መፍቻ የሚሆኑ ዳሰሳዎችን የመስራት እንዲሁም የኢኖቬሽንና ስታርት አፕ ስትራቴጂዎችን የመቅረጽ ተግባርን ያከናውናል። እነዚህ ድጋፎችም ማዕከላቱ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ባህልን በማጎልበት ረገድ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ሰዎች ለማሳደግና ወደ ገበያ ለማምጣት የሚያደርጉትን ጥረት በተሻለ ብቃት ለመፈፀም ያግዟቸዋል ሲሉ ያብራራሉ።

በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የምርምርና ልማት ዘርፍ በሀገር ውስጥም ይሁን በውጭ የሚገኙ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የሚያስችል የዕውቀትና የክህሎት አቅም እንዲሁም የአመለካከት ውስንነት በስፋት የሚስተዋል በመሆኑ የቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከላቱ ብዙ ተግዳሮቶች ያጋጥሟቸዋል ሲሉም ይጠቁማሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ቀደም ሲል በሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ግልጽ ግብ ያለውና ወጥ የሆነ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ከማስፈን አኳያ የአሠራር ሥርዓት ክፍተቶች ነበሩ። በግዥም ሆነ በምርምር የሚገኝ የቴክኖሎጂ ዕውቀትን ለማሰባሰብ፣ ለማከማቸት እና ለማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት አለመኖሩ ሀገሪቱ ቴክኖሎጂና ዕውቀትን



ለማከማቸትም ሆነ ከተከማቸው ዕውቀት የሚገባትን ጥቅም ማግኘት አልቻለችም። በተጨማሪም የቴክኖሎጂ ሽግግር ስልቶችን ከመለየት ጀምሮ እስከ አጠቃቀም ድረስ በርካታ ክፍተቶች ነበሩ። ይህ ደግሞ ቴክኖሎጂ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ፈጠራን በመጨመርና ቀጣይ ቴክኖሎጂዎችን በማበልፀግ የተሻለ እሴት ለመፍጠር የሚያስችል ሁኔታ እንዳይኖር አድርጓል።

የአንድ ሀገር ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ሊያድግ የሚችለው ምርታማ የሆነ ኢኮኖሚ መገንባትና በርካታ ተወዳዳሪ ኢንተርፕራይዞችን መፍጠር ሲቻል ነው። ይሁን እንጂ ኢንተርፕራይዞችን ለመፍጠርም ሆነ በተለዋዋጭ የቢዝነስ ከባቢ ውስጥ ተላምደው መጓዝ እንዲችሉ የሚያግዝ የኢኖቬሽን ሥነ-ምህዳር ስላልተገነባ በሀገርም ሆነ በዓለምአቀፍ ደረጃ ብቁ እና ተወዳዳሪ መሆን የቻሉ ኢንተርፕራይዞችን በበቂ መጠን መፍጠር አልተቻለም። ይህ የዘርፉ ክፍተት ደግሞ በቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከላት ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ጫና ፈጥሮ ቆይቷል።

አዲሱ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ የኢንኩቤሽን ማዕከላት እንዲጠናከሩ ምቹ ሁኔታዎችን እንደሚፈጥር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ገልጿል። ፖሊሲው ጀማሪ ተቋማት እና የኢኖቬሽን ሥርዓተ-ምህዳር ገንቢዎች (STI Incubation Centers) የፋይናንስ፣ የቴክኒክ፣ የመስሪያ ቦታ እና መሰል ድጋፎችን የሚያገኙበት፤ ለጀማሪ ተቋማት (Technology Startups) የገበያ ዋጋ ትመና እና የኢንቨስትመንት እድል የሚፈጠርበት፤ ስትራቴጂካዊ ተፈላጊነት ባላቸው የቴክኖሎጂ መስኮች የግልና የመንግስት አጋርነት የሚኖርበት፤ በጥናት ላይ የተመሠረተ የእሴት ሰንሰለት እና የኢኖቬሽን ክላስተሪንግ ስርዓት የሚስፋፋበት እንዲሁም ውጤታማነታቸው የተረጋገጠና ወደ ምርትና አገልግሎት የተቀየሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን የሚያበረታታ የግዥ ሥርዓት የሚዘረጋበት የአሰራር ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል።

በፖሊሲው ላይ እንደተመለከተው፣ ከመሰረታዊ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የተቃኘ መሰረታዊ የሰው ሀብት ልማት እንዲገነባ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ መጪውን ጊዜ ማዕከል ያደረገ የሰው ኃይል እንዲገነባ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሰራ ይደረጋል። በዚህም የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን እንቅስቃሴን በብቃት መምራት የሚችል የሰው ኃይል ይገነባል። ከዚህ በተጨማሪም ከመደበኛው የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች በተጓዳኝ ለዜጎች የተለያዩ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ባህል ግንባታ ሊፈጥሩ የሚችሉ የማህበረሰብ ልማት ተግባራት ይከናወናሉ።

ከዚህ በተጨማሪም የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትንና የዕውቀት ሽግግሩን ለማሳለጥ የቴክኖሎጂ ልማት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የምርምር እና ስርፀት ዩኒቶች (Technological Research Units) በማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲቋቋሙ ድጋፍ እንደሚደረግ፤ ሀገርን ምርታማና ተወዳዳሪ ለሚያደርጉ ቴክኖሎጂዎች ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራ እንዲሁም ሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀምና ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት እንደሚዘረጋ በፖሊሲው ላይ ተመላክቷል። የኢኖቬሽን ሥነ-ምህዳር በመፍጠርና የሃገሪቱን የኢኖቬሽን አቅም በማዳበር ኢኖቬሽንን በሰፊው ለልማትና ሰፊ የሥራ ዕድሎችንና ሀብቶችን ሊፈጥር በሚችል መልኩ፣ በሀገርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ በርካታ ኢንተርፕራይዞችን ለመፍጠር ይሰራል።

ፖሊሲው የግል ኢንኩቤሽን ማዕከላት የመሪነት ሚና እንዲጫወቱ እና በራሳቸው የሚንቀሳቀሱበትን አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑንም የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ገልጿል። በዚህ ረገድ ጀማሪ ተቋማት እና የኢኖቬሽን ሥርዓተ-ምህዳር ገንቢዎች የፋይናንስ፣ የቴክኒክ፣ የመስሪያ ቦታ እና መሰል ድጋፎች የሚያገኙበት የአሰራር ሥርዓት እንደሚዘረጋ፤ ኢንተርፕራይዞች ቴክኖሎጂን መሰረት አድርገው ምርታማነትን እንዲያሳድጉ የሚደግፉ ልዩ ተቋማት እንደሚመሰረቱ እንዲሁም አምርተው ወደ ዉጪ ለሚልኩ፣ የገቢ ምርትን ለሚተኩ እንዲሁም ወደ ሌሎች ሃገራት ለሚስፋፉ የቴክኖሎጂ ኢንተርፕራይዞች ድጋፎችና ማበረታቻዎች እንደሚደረጉ ፖሊሲው ያሳያል።

በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሥራዎች የግሉ ዘርፍ ሚና ከፍተኛ መሆን እንዳለበትና የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማትና ተሳትፎ እያደገ እንዲሄድ የግሉ ዘርፍ በቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር፣ በኢኖቬሽን ልማት እንዲሁም በምርምር ሥራዎች ላይ የመሪነት ድርሻ እንዲኖረው እንደሚጠበቅ የሚጠቅሰው ፖሊሲው፤ ዘርፉ በመሠረተ-ልማት ሥራዎች፣ በሀብት ምደባ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ስለሚኖረው በመንግስት ይተገበሩ በነበሩ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የልማት ሥራዎች ላይ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እያደገ እንዲሄድ እንደሚደረግ ያመላክታል።

በፖሊሲው ላይ እንደተመለከተው፤ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግ «ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት ተደራሽ፣ አካታችና ቀልጣፋ የፋይናንስ አቅርቦት አማራጮች ይዘረጋሉ፤ ለሳይንሳዊ ምርምር፣ ለቴክኖሎጂ ልማትና፣ ለኢኖቬሽን እንዲሁም ለቴክኖሎጂ ግብይት የሚውሉ ፋውንዴሽኖችና ፈንዶች ይቋቋማሉ፤ኢኖቬተሮችንና ኢንተርፐረነሮችን ለማበረታታት የሚያስችል እንዲሁም ለኢኖቬሽን ልማት ሥራዎች የግሉ ዘርፍ ከመንግስት በቀጥታ የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኝበት አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፤የተመራማሪዎች ማበረታቻ ስርዓትም ይተገበራል። በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ዘርፍ ለተሰማሩ ኢንቨስተሮች ልዩ ልዩ የታሪፍ፣ የታክስ እና ተዛማጅ የፋይናንስና የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች እንዲሰጡ እንዲሁም ለዘርፉ ዕድገት የላቀ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ተዋናዮች እንዲበረታቱ ይደረጋል» የሚለው በፖሊሲው ላይ ተገልጿል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## ግራጫ ጦርነትን ለመቋቋም - ሕዝብን ከጎን ማሰለፍ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሰኔ 30/2014 በህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ለቀረቡላቸው በርካታ ጥያቄዎች በየፈርጁ ምላሽ እና ማብራሪያ መስጠታቸው ይታወሳል። በተለይም በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ስለሚስተዋለው የሠላም ሁኔታ በርካታ ምሳሌዎችን በማጣቀስ ማብራሪያ ሰጥተዋል። የሀገሪቱን ሠላምና ደህንነት አስመልክቶ ከሰጧቸው ማብራሪያዎች መካከልም የሀገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ ተጠቃሽ ሲሆን፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን በማጣቀስ አስረድተዋል።

በሰላምና ደህንነት ዙሪያ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የሰጡት ማብራሪያ ላይ ሐሳባቸውን የሰነዘሩት የዘርፉ ምሁራን በበኩላቸው፤ እውነታውን በግልጽ ይፋ በማድረግ የህዝብን ድጋፍ መያዝና ህዝብ በሠላም ሁኔታ የመኖር መብቱን ማስጠበቅ እንዲሁም ወቅታዊ መረጃዎችን በወቅቱ ለዜጎች በመስጠት ሀገሪቱን ከጫና ማላቀቅና ህዝቡን ከጎኑ ማሰለፍ የመንግስት ኃላፊነት መሆኑን መገንዘብ ያሸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ስለ ሀገሪቱ ወቅታዊ ሠላም እና ደህንነት አስመልክቶ፤ ‹‹በብዙ መንገድ ኢትዮጵያ ላይ አሁን እየተካሄደ ያለው ጦርነት የግራጫ ጦርነት ነው። ነጭ መዝገብ ላይ ወይም ጥቁር መዝገብ ላይ የተቀመጠ ሳይሆን የግራጫ ጦርነት ባህሪ ነው ያለው›› ሲሉ ለህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አባላት ሐሳባቸውን ገልጸዋል።

በማብራሪያቸውም ወቅት፤ የግራጫ ጦርነት ሲባልም አንደኛው የመረጃ ጦርነት መሆኑን አብራርተዋል። ይህንንም በምሳሌ አስደግፈው ሲናገሩ፤ በወለጋ አንድ ቀበሌ ውስጥ ነገ ሞት የሚካሔድ ከሆነ በብዙ ዓለም ያሉ የመረጃ ተዋናዮች ያውቁታል። ልክ ሞት እንደተከሰተም የዓለም ሚዲያዎች ይዘግባሉ። እኛ ገና መረጃውን ሰምተን ወታደርን በምናሯሯጥበት ጊዜ የመረጃ ጦርነቱ አካል ስለሆነ ከእኛ በላይ አጀንዳውን ማስፋት የሚችል ኃይል አለ ብለዋል።

ሁለተኛው ሰላምን የማወክ ስራው ዲፕሎማሲ ተኮር ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ‹‹ዳታውን ላለማጋነን ፈርቼ እንጂ በአደጉ ሀገራት ግድያ ያለው በየደቂቃው ነው ብለዋል። ሀገራት በየቀኑ ሰው ይሞትባቸዋል፤ በምንም መመዘኛ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለፈው ዓመት ተደምሮ ወደ ቁጥር ከመጣን በጣም ጥቂት ነው። እዚያ ግን የሀገሬው ሚዲያ ከሚያወራው ውጭ አጀንዳ ስለማይሆን፤ እኛም ዘንድ ስለማይደርስ፤ በየቀኑ ሰው እየሞተባቸው ያሉ ሀገራት ሳይቀር ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ጉዳይ አስጨንቋቸው የዓለም ሚዲያ አጀንዳ እንደሚያደርጉት ነው የተናገሩት ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በከተማቸው ሰው እየሞተ፤ ልጆቻቸው እየሞቱ፤ ያን መከላከል ሳይችሉ የእኛን ጉዳይ ግን የዓለም አጀንዳ ማድረግ ይፈልጋሉ›› ሲሉ ለህዝብ እንደራሴዎች ማብራራታቸው ይታወሳል። ከዚህ በተጨማሪም የሳይበር ጦርነት እና የተልዕኮ ውጊያም የአፍራሽ አካላት ሚና መሆኑን ዶክተር ዐቢይ አብራርተዋል።

ታዲያ ይህን የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግር ከምሁራን እይታ አኳያ እንዴት ይታያል ሲል የዝግጅት ክፍላችን ለምሁራኑ ላቀረበላቸው ጥያቄዎች ንግግሩን በተመለከተ ሙያዊ ማብራሪያ ከሰጡት መካከል አንዱ የህግ ባለሙያው አቶ በፍርዴ ጥላሁን ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በህዝብ እንደራሴዎች ለቀረበላቸው ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ ከሞላ ጎደል መልካም የሚባል ነው፤ ነገር ግን ብዙ መስተካከል የሚገባቸው ነገሮችም አሉ። ከዚህም ውስጥ በተለይም በአደጉት ሀገራት የሆነውን የወንጀል ድርጊት ከኢትዮጵያ ጋር ለማነፃፀር የተሄደበት መንገድ አግባብ አለመሆኑ ተጠቃሽ ነው።

ለዚህም ማብራሪያ ሲሰጡ እንደተናገሩት፤ በአደጉት ሀገራት በብዛት የሚሰማውና እየተከናወነ ያለው የጅምላ ጭፍጨፋ ሳይሆን እየተፈጸመ ያለው በህገ ወጥ መንገድ በታጠቁት የጦር መሳሪያ አጠቃቀም የመነጨ ጋጠ-ወጥነት ነው። አሊያም በአደንዛዥ ዕፅ በከፍተኛ ሁኔታ በመጠቀምና በመጦዝ ወይንም በአዕምሮ መታወክና ግልፍተኝነት የሚፈፀም ወንጀል ነው።

ይህም ቢሆን በህግ አግባብ መስመር ለማስያዝ አቅም

**የዜጎች ሞት የፖለቲካ ነጥብ ለማስቆጠር የሚነሳ ሳይሆን ለሁሉም አካል የጋራ ህመም ስለመሆኑና ሰብዓዊነት ላይ የተፈጸመ በመሆኑ በጋራ በመቆም መኮነን ይገባል። እውነታውን በግልጽ ይፋ በማድረግ የህዝብን ድጋፍ መያዝና የህዝብን በሠላማዊ ሁኔታ የመኖር መብት ማስጠበቅ የመንግስት ኃላፊነት መሆኑን መገንዘብ ይገባል**



መገንባታቸውን የገለጹት የህግ ባለሙያው አቶ በፍርዴ፣ በፍርድ አደባባይም እንደሚያቆሙት አስረድተዋል። ይሁንና በኢትዮጵያ ውስጥ እየተከሰተ ያለው ደግሞ በተወሰነ አካባቢ ላይ ያነጣጠረ ተደጋጋሚ ግድያና ማፈናቀል እንደሆነ ጠቅሰው፤ ይህን አስመልክቶ የህዝብ እንደራሴዎች ላነሱት ጥያቄ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሰጡት ምላሽ አጥጋቢ እንዳልሆነ ነው የተናገሩት።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ በተለያየ ቦታ በጅምላ የሚሞቱት ሰዎች በመሆናቸው ብቻ በሰብዓዊነት ሁሉም በጋራ ድርጊቱን ሊያወግዘው እና ሊቆጣጠረው ይገባል። ይሁንና አማራ ሲሞት አማራ ብቻ የሚቆረቆር እና የሚጠይቅ፤ ሌላው ብሄር ሲሞት ደግሞ የብሄሩ ተወላጅ ብቻ ሊያወግዘው ወይንም ሊቆረቆር አይገባም። ይልቁንም ይህ በሰው ልጆች ላይ የተፈፀመ ወንጀል መሆኑን በማመን በአንድነት ማውገዝ ይገባል።

የዜጎች ሞት የፖለቲካ ነጥብ ለማስቆጠር የሚነሳ ሳይሆን ለሁሉም አካል የጋራ ህመም ስለመሆኑና ሰብዓዊነት ላይ የተፈጸመ በመሆኑ በጋራ በመቆም መኮነን ይገባል። እውነታውን በግልጽ ይፋ በማድረግ የህዝብን ድጋፍ መያዝና የህዝብን በሠላማዊ ሁኔታ የመኖር መብት ማስጠበቅ የመንግስት ኃላፊነት መሆኑን መገንዘብ ይገባል ብለዋል። የህግ ባለሙያው ከዚህም በዘለለ ስለሁኔታው ማብራራት ብቻ ሳይሆን ይቅርታ መጠየቅንም ያካትታል ባይ ናቸው።

የሀገሪቱ ህገ-መንግስት የሁሉም ገዢ በመሆኑና በሁሉም ቦታ ገቢራዊነቱ መረጋገጥ ስላለበት የህዝብ እንደራሴዎችም ይህን በማረጋገጥ ረገድ ሚናቸውን ሊወጡ ይገባል። ከአንዱ ጫፍ ያለው አዋጅ ሆነ መመሪያ የሁሉም እና የጋራ ስለመሆኑም ሊጤን እንደሚገባ ባለሙያው ያስገነዝባሉ። ይህ ካልሆነ ግን ችግር ፈጣሪዎች ቦታ እና ሁኔታዎችን እየቀያየሩ መቀጠላቸው አይቀሬ ነው የሚል እምነትና ሙሁራዊ ምልከታ እንዳላቸው አመልክተዋል።

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር እና ጥረት በተጨማሪም የማህበራዊ ሚዲያ እና ማህበረሰብ አንቂዎች የሚሄዱበት መንገድ ሀገሪቱን ከችግር ለማላቀቅ የራሱ የሆነ ሚና አለው። በተለይም ደግሞ ሀገሪቱን በአሁኑ ወቅት ለመታደግ መጥፎ ዜናዎችን ሆን ብሎ ከማሰራጨት በመቆጠብ አቀራረቢ ሐሳቦች ላይ ማተኮርም አንዱ መፍትሄ መሆኑን ባለሙያው ያብራራሉ። እነዚህ ሚዲያውን የሚዘውሩ አካላት ገንዘብ የመስራት ፍላጎታቸውንም መጥፎ ነገሮችን ከማውራት ይልቅ በመልካም ነገሮች ላይ በመንተራስ ገንዘብ ማግኘት እንዳለባቸውም ማጤን እንዳለባቸው ያመለክታሉ። ነገር ግን ችግሮችን በማድበስበስ እና በመሸፋፈን ማለፍ በቀጣይ ችግሮችን የበለጠ ሊያወሳስብ ስለሚችል የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚገባም ነው የሕግ ባለሙያው አቶ በፍርዴ የሚያሳስቡት።

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር አቶ እንዳለ ንጉሴ በበኩላቸው፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለዲፕሎማሲ ጦርነት ያነሱት ጉዳይ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ትልቁ የጦርነት መሳሪያ ስለመሆኑ ይናገራሉ። በርካታ ሀገራት በቀጥታም ይሁን በእጅ አዙር ምኞታቸውንና ፍላጎታቸውን ለማሳካት ይህን ስልት እንደሚጠቀሙ ይገልጻሉ።

እንደ አቶ እንዳለ ገለፃ፤ የዲፕሎማሲ ጦርነት ምዕራባውያኑ የተካኑበት ሲሆን፣ ፍላጎታቸውን በአቋራጭ ለማግኘት እና ያለሙትን ደግሞ በሌላው ላይ ለመጫን ይጠቀሙበታል። በዚህም ዓለም አቀፍ ተቋማት ጭምር ተናበው የሚሰሩበት ነው። በዚህ የግራጫ ጦርነት በርካቶችን መጉዳታቸው ይነገራል። እነዚህ ሀገራት ይህን ስውር ሴራ ሲሠሩ ደግሞ ብቻቸውን ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነት ያላቸውን የመገናኛ ብዙሃን አውታሮችንም ጭምር በመያዝ ነው።

ዓለምአቀፍ ተቋማት በግራጫ ጦርነት እና የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ዓለም ምስቅልቋል አውጥተዋል ይላሉ። ለአብነትም ሶሪያ፣ ሊቢያ፣ ኢራቅ እና በርካታ ሀገራትም የፈረሱት እና እየፈረሱ ያሉትም በዚህ የተናበበ አካሄድ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሰሞኑን የሱዳን ትንኮሳን አስመልክቶ የምዕራባውያን ሚዲያዎች ሲሰጡት የነበረው ሽፋን የግራጫ ጦርነቱ አንድ አካል መሆኑን ይናገራሉ። ከዚህም በተጨማሪ የአውሮፓ ህብረት ህዳሴ ግድብን አስመልክቶ የግብፅ ጥቅም መነካት የለበትም በማለት ያወጣው መግለጫ ሚዛናዊነት የጎደለው ከመሆኑም በተጨማሪ ግራጫ ጦርነት አንዱ መልክ ነው ሲሉ ተናግረዋል። ይህንንም ለማድረግ የተፈለገው ዓላማቸውንና ፍላጎታቸውን ለማሳካትና ኢትዮጵያን ጫና ውስጥ ለማስገባት በማሰብ እንደሆነ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያን ጫና ውስጥ በዲፕሎማሲ እና ግራጫ ጦርነት በተባለው ስልት ለመጠቀም ብዙ ጥረት መደረጉን አክለውም ተናግረዋል። ህብረቱ ለዚህም ይረዳው ዘንድ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በተፈጠረው ጦርነት በርካቶች ለሕወሓት በመወገን መንግስትን ሲወቅስና ሲተች ነበር። ይሁንና ይህን ለማድረግ የዳዱት እውነታውን ስለሚያውቁት ሳይሆን ለዘመናት ሀገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም ለግለሰቦች ብሎ አሳልፎ የሰጠውን ሕወሓትን ለመታደግ እና ወደ መንበሩ ለመመለስ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ለ40 ዓመታት በኢትዮጵያ ላይ ተሰርቶ የነበረው ሴራ በመክሸፉ ለዚህ መነሳሳት እንደ ምክንያት ይሆናቸዋል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት ዓለም ሁሉ ትኩረቱ ዩክሬን ላይ ሆኖ ሳለ የኢትዮጵያን ጉዳይ ግን በዋናነት መያዙም በቀላሉ መታየት የለበትም የሚሉት አቶ እንዳለ፣ የምስራቅ አፍሪካ ጉዳይ ሌላኛው የትኩረት መስክ በመሆኑ ነው ይላሉ። በተለይም ደግሞ በቀጣናው የኢትዮጵያ ሚና የላቀ በመሆኑ ትኩረታቸውን አሁንም ድረስ እንዳሳረፉበት ተናግረዋል። ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵውያን ከዚህ ጫና ለመላቀቅ ግን አንዳች ነገር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ምክራቸውን ለግሰዋል።

በተለይም አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኢትዮጵያን ለመጉዳትና ጫና ለማሳደር በሚሯሯጡበት ወቅት በሀገር ውስጥ ተባባሪ ሆኖ መገኘት የለባቸውም ይላሉ። ህብረተሰቡም ቢሆን በተለያዩ አካላት የሚሰጡ መረጃዎች በሙሉ ትክክል ናቸው ብሎ ከመቀበል ይልቅ ጉዳዮችን በጥልቀት መመርመር እና ሀገራዊ ጥቅምን ማስቀደም ይጠበቅባቸዋል። በተለይም ደግሞ ኢትዮጵያ ወደ ከፍታ ለመጓዝ በምታደርገው ሂደት ተፃራሪ የሆኑ አካላትን መጠቀሚያ ከመሆንም መጠንቀቅ ይገባል። መንግስትም ወቅታዊ መረጃዎችን በወቅቱ ለዜጎች በመስጠት ሀገሪቱን ከጫና ማላቀቅና ህዝቡን ከጎኑ ማሰለፍ አለበት ባይ ናቸው።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የትምህርትን ስኬት ከሥራ ፤ትዳርና ልጅ ጋር ያቀናጁ ጀግኒቶች

**ሰላማዊት ውቤ**

ትምህርትን በሥራ ፣ በትዳርና በልጆች ጫና መካከል ሆኖ መማር እጅግ ፈታኝ ነው። ብዙ ጊዜ በእንዲህ ዓይነት ተደራራቢ አጣብቂኝ ውስጥ አልፎ ትምህርትን ካሰቡበት ዳር ማድረስም ጀግንነትን ይጠይቃል።

አብዛኞቹ ሰዎች መማር እየፈለጉ የማይሞክሩት ለዚሁ እንደሆነ አጫውተውናል። ደፍረው የሞከሩትና የዘንድሮ ዓመት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተለያየ ትምህርት ክፍልና መርሐ ግብር ተመራቂ ሴት ተማሪዎች ጫናው ከባድ ቢሆንም ይቻላል ብለው ከገቡበት ለስኬት መብቃት እንደሚቻል አሳይተዋል። እኛም በዛሬው በሴቶች ዓምዳችን ያልሞከሩት እንዲሞክሩት ብርታትና አቅም ሊሆን ይችላል ያልነውን የነዚህ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዘንድሮ ዓመት ስኬታማ ሴት ተመራቂዎችን ተሞክሮ ልናጋራችሁ ወደናል።

ተመራቂ ተማሪ ግርማዊት አበራ ዘንድሮ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተከታታይ (ኤክስቴንሽን) ትምህርት መርሐ ግብር ካስመረቃቸው ተማሪዎች መካከል አንዷ ናት። በጀንደር ስተዲ በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀችው ፎር አምጥታ ነው። እሷ እንደምትናገረው ይሄ ደግሞ ሴቶች ትምህርታቸውን መከታተል ብቻ ሳይሆን በአጥጋቢ ውጤት ማጠናቀቅ መቻላቸውንም ያረጋግጣል። በትምህርት ሂደት የገጠማት ፈተና ቀላል ባይሆንም በጥሩ ውጤት ለማጠናቀቅ መብቃቷ ለሌሎች እንደ እሷ በፈተና ውስጥ ላሉና ፈተናውን ለማለፍ ፈራ ተባ የሚሉ ሴቶች ቁርጠኝነትን የሚያስታጥቅ አርአያ ይሆናል ብላ ታስባለች ።

ተመራቂ ትዕግስት ፍቃዱም በዚሁ ትምህርት መስክ ነው በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀችው። ትግስት ባለትዳርና የሁለት ልጆች እናት ናት። ደግሞ በአንድ የመንግስት ተቋምም ትሰራለች። ከትዳር ከልጅና ከሥራ በተጨማሪም የተለያዩ የቤት ውስጥ ኃላፊነቶችም አሉባት።

ትዕግስት ባለፈው ቅዳሜ በጀንደር ስተዲ መስክ ልትመረቅ የቻለችበትን የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቷን የዛሬ ሦስት ዓመት የጀመረችው በዚህ ሁሉ ጫና ውስጥ ሆና ነው። ትምህርቱን የጀመረችው የመጀመሪያ ዲግሪ ፤ እንዲሁም የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቷን ካጠናቀቀች ከ12 ዓመት በኋላ እንዲሁም ትዳር ከመሰረተች ከ10 ዓመት በኋላ ነው ። በተጨማሪም ትምህርት ቤት ስትገባ ወንዱና ትልቁ ልጇ የአምስት ሴቷ ልጇዋ ደግሞ የአንድ ዓመት ነበሩ። ዕድሜያቸው እሷን አብዝተው የሚፈልጉበት በተለይ ትንሽዋ ገና ጡት ያልጣለችበት ነበር።

ሆኖም ባለቤቷ ትምህርቷን እንድትማር ከማነሳሳትና ከማበረታታት ጀምሮ ልጆቹን በመከታተሉ ከፍተኛ ድጋፍ ሲያደርግላት ቆይቷል። በተለይ ትልቁ ልጅ ለትምህርት ከደረሰ በኋላ ትምህርት ቤት እንዲሄድ በማድረጉና ምን ላይ እንዳለ በማጤኑ ረገድ ያደረገላት ድጋፍ የጎላ ነው። ከልጆቹ ባሻገር የቤቱን ኃላፊነት በመጋራቱም ቢሆን ያደርግላት የነበረው አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚታይ አልነበረም።

‹‹ባለቤቴ ባያግዘኝና ባያበረታታኝ ፍፁም ልጀምረውና ልጨርሰው አልችልም ነበር›› ስትልም የክብደቱን ኃያልነት ገልፃዋለች። ትዕግስት እንዳጫወተችን በሥራዋ በኩል እጅግ የበዙ ተደራራቢ ኃላፊነቶች አሉባት። ሥራዋ ቶሎ ቶሎ መስክም ያስወጣታል። በዚህ መካከል ቅዳሜን ጨምሮ በሳምንት ሁለት ሙሉ ቀን ትምህርት ተምሮ መመረቅ ይከብዳል። ለእንደ እሷ ዓይነት ጫና ለበዛባቸው ሴቶች ላይታመን የሚችል እጅግ ፈታኝም ነው። በዛ ላይ ውድድሩ ጠንከር ያለ ነበር።

የጀንደር ስተዲ ኮርሶችም ቢሆኑ አዲስ ናቸው ትላለች ትዕግስት፤ የትምህርት ሂደቱን የክብደት መጠን ስትገልፀው። ይሄም ብቻ አይደለም አዝወትራ መስክ በምትሄድበት ጊዜ የሚያልፏት ፈተናዎችና የማትከታተላቸው የትምህርት ክፍለ ጊዜዎች እጅግ ብዙ ነበሩ። በዚህ በኩል ደግሞ የክፍል ጓደኞቿ አግዘዋታል። ያለፏትን ፈተናዎች በሜካፕ መውሰዷም በእጅጉ ረድቷታል።

‹‹ሆኖም በነዚህ ሁሉ በመታገዝና በግሌም ከጠበኩት በላይ በመጣር ትምህርቴን በጥሩ ውጤት ለማጠናቀቅ በቅቻለሁ ብላናለች ያመጣችው ነጥብ ከትምህርት ክፍሉ ፎር ከዘጋችው የማይተናነሰው ተማሪ ትዕግስት።

ሌላዋ የዩኒቨርሲቲው ማስተርስ ኦፍ ቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ተመራቂ ተማሪ እመቤት ረጋሳ ናት። የተማሪዎች ተወካይ ኃላፊም የሆነችው እመቤት የመጀመሪያ ዲግሪዋን በመደበኛው የትምህርት መርሐ ግብር በፕሎሶፊ መያዟን ትጠቅሳለች። እመቤት እንደ ትምህርት ክፍሉ ትምህርት የጀመሩት 2011 ግማሽ ሴሚስተር ላይ መሆኑንም ትናገራለች። ባለፈው ቅዳሜ የያዘችው የሁለተኛ ዲግሪዋ በተጨማሪ በሌላ የትምህርት መስክ ሁለተኛ ዲግሪ ቀደም ሲል ይዛለች፡፡ በቅርቡም ሦስተኛውን በፖለቲካል ሳይንስ ሶስተኛ የማስተርስ ዲግሪ ለመያዝ እየተማረች መሆኑን ታወሳለች ።

አሁን ላይ የምሰራው ውሜን ኢንፖወርመንት ላይ በመሆኑ ሥራዬ ከትምህርቴ ጋር ይገናኛል። ራሴን አርአያ ማድረግ እፈልጋለሁ። በመሆኑም ሌላ ሦስተኛ ማስተርስም በፖለቲካል ሳይንስ እየተማርኩ ነው ትላለች እመቤት። እንዳከለችው የጀንደር ባለሙያ እንደመሆኗ ሴቶች ተምረው ብቁ ሆነው ካልተገኙ የራሳቸውን ችግር መፍታት አይችሉም። ራሳቸውን ለመቻልና ያለባቸውን ጫና ለማስተካከል የግድ መማርና ራሳቸውንም መቻል አለባቸው የሚል አቋም አላት። ከዚህ ተነስታ ለጾታ አጋሮቿ እራስን ማበርታት እንደሚገባም ትመክራለች ።ሴት ስለሆንኩ ብዬ እጄን መስጠትና ለራሴ ይቅርታ ማድረግ አልፈልግም። ምክንያቱም መጀመሪያ እኔ ካልተማርኩና ካልተለወጥኩ የሌላዋን ሴት ሕይወት መለወጥ አልችልምና ትላለች። ችግር ለመፍታት በችግሮች እየተፈተኑ ማለፍንም እንደሚጠይቅ የራሷን ተሞክሮ ዋቢ አድርጋ ታካፍላለች ። ፈተናው ከቤት ስትጀምረው ቤት ውስጥ በተለይ ሴት ሲኮን ልጆች ከመንከባከብና ቤት ከመምራት ጀምሮ ብዙ ኃላፊነቶች ይኖራሉ። ባለቤቷ በሀሳብም ሆነ የቤቱን ኃላፊነት በመሸፈንም በብርቱ ሲያግዛት ነው የቆየው። እንድበረታ ፤ እንዳጠና አጥንቼና ተዘጋጅቼ ለፈተና እንድቀርብ ያበረታታኝም ነበርም፡፡ ልጆቻችንን ትምህርት ቤት ከመውሰድ በተጨማሪ አጠቃላይ የሚከታተላቸውም እሱ ነበር። በዚህ በኩል ነፃነት ሰጥቶኛል ብላናለች። እንደ እመቤት ትምህርቷን ለማጠናቀቅ የሄደችበት ሂደት በራሱ ፈተና የበዛበትና አስቸጋሪ ነበር። ትምህርቱም ትንሽ የሚከብድና ጊዜ የሚፈልግ ሆኖ አግኝታዋለች። አብዝቶ ማጥናትንና ሌሊት ተነስቶ መሥራትም ይጠበቅባት ነበር። ብዙ ጊዜም በትምህርት ሰዓት መስክ የምትወጣበት ጊዜም ቀላል አልነበረም። ሆኖም አስተማሪዎቻቸው በትምህርት ክፍለ ጊዜ መቅረቷን ስለማይፈልጉ በጣም ትችገር ነበር። ይሄን ሁሉ ከትምህርቱ ጋር አቻችሎ መወጣትም ይፈልግ እንደነበር ታወሳለች። እሷ ደግሞ ችግሩን መወጣት አልችልም ብሎ ወደ ኋላ ሳይቀሩ ጨክኖ መማር እንዳለባት አምና ስለገባች ለውጤት በቅታለች።

በመሆኑም በአጋጣሚ የተማሪዎች ተወካይ ነበረችና ጫና ሲመጣባቸው ከመምህራኖች ጋር የሴት ተማሪዎችን ጊዜ በማመቻቸት ጫናውን ለመቀነስ ስትሞክር ቆይታለች። ከተማሪዎች ጋር በመነጋገር መምህራኖችን በማሳመንም ሰርታለች። የፈተና ስኬጁል በጣም ሲቀርብም ስኬጁሉን ከሚያዘጋጁት ጋር በመነጋገር ቀኖች እንዲያራዝሙላቸው ታደርግ ነበር። ተወካይ መሆኗ በግሏ በዚህ መልኩ ጠቅሚታል። ሌሎች እንደ እሷ ጫና ያለባቸውን ሴቶችም መጥቀሙን ማስተዋል ችላለች።

እኛ ሴቶች በተለይ በትዳርና በሥራ ዓለም ከገባን በኋላ በሚገጥሙን ድርብርብ ኃላፊነቶች መማር እስከፈለግንና እስከሚገባን እንድንማር በማድረግ በኩል የትዳር አጋሮቻችን ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው።

የኔ ባለቤት አቶ አማኑኤል ደስታ በዚህ በኩል የአንበሳውን ድርሻ በመወጣቱ ዛሬ ትምህርቴን በተገቢው መንገድ በመከታተል 3 ነጥብ 53 አጥጋቢ ውጤት አምጥቼ ለመመረቅ በቅቻለሁና እጅግ አድርጌ አመሰግነዋለሁ ያለችን ደግሞ ተመራቂ ተማሪ ሳራ ወልደአማኑኤል ናት።

ሳራ እንደነገረችን የመጀመሪያ ዲግሪዋን በዚሁ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢንፎርሜሽን ሲስተም በመያዝ ነው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን የተቀላቀለችው። ሳራ የሶስት ልጆች እናትና ባለ ትዳር ነች።ባለቤቷ አቶ አማኑኤል ደስታ ጎልታ እንድትወጣ ይረዳት ነበር። ትምህር ቤት ገብታ ሁለተኛ ዲግሪዋን እንድትይዝ በጣምም አበረታቷታል። እሱ ስለረዳኝም ነው የተማርኩትና የጨረስኩት የምትለው ሳራ በአንድ ዓለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ እንደምትሰራም አጫውታናለች።

የምትሰራው ሥራ ብዙ መስክ የሚያስወጣ ባይሆንም ቢሮ ውስጥ ፋታ አይሰጣትም። ትምህርቷን በርቀት ትምህርት መርሐ ግብር ስትከታተል የነበረችውም ለዚህ ነው። ቲቶርያል ክላስ መከታተሉ፤ ሙጁል ማንበቡ እጅግ ሰፊና የተረጋጋ ጊዜ የሚፈልግ ነበር። በዚህ ላይ የዋናው ፈተና ሰሞን የመጨረሻ ልጇን ልትወልድ መቃረቧ ጫናውን ከማክበድ አልፎ እመረቃለሁ የሚለውን ተስፋዋን አጠራጣሪ አድርጎባት ነበር። ከዚህ ጋር ቢከብዳትም ባለቤቷ ልጆቻቸውን መከታተሉን ጨምሮ የቤት ውስጥ ኃላፊነቶችን ስለሸፈነላት ልትወጣው ችላለች። ትምህርቱን ኮቪድ ከመግባቱ ከአንድ ዓመት በፊት መጀመሯን የምታወሳው ሳራ፤ ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀሙ ትምህርታቸው ሳይቋረጥ በየቤታቸው ሆነው እንዲከታተሉ ማስቻሉንና በእሷ ላይ የሚደርሰውን ጫና በእጅጉ የቀነሰላት መሆኑን ታወሳለች።


በባለቤቷ እገዛና በእርሷ ጥንካሬ ዛሬ ላይ ትምህርቷን አጠናቅቃ ለምረቃ በቅታለች ። ይሄ ጥሩ ውጤት ነው።ከእግዚአብሄር እርዳታ ጋር ባለቤቴ ደግፎኝ ጨርሻለሁ።ትምህርት የመለወጥ መሣሪያ ነው። የተማረች ሴት መሆን ከራስ ጀምሮ ለቤተሰብና ለአገር ትልቅ ጥቅም አለው። በመሆኑም የሚፈልጉትን ያህል በትምህርት ሳይገፉ እንደ እሷ በሥራ፤በትዳርና ልጅ የተጠመዱ ሴቶች የፈለገውን መስዋእትነት ከፍለው መማር እንዳለባቸውም ትመክራለች። ሴቶች ሲማሩ የነሱን ያህል የተማሩትም ሆነ ያልተማሩት የባለቤታቸው ድጋፍ ከሌላቸው ስኬታማ አይሆኑም።

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ባለፈው ቅዳሜ በምርቃት ስነስርዓቱ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉልን መልዕክት እንዳሉት፤ መማር ማለት የባህርይ ለውጥ ማምጣት ነውና የትዳር አጋሮች እባካችሁ ሚስቶቻችሁን እንደ እኔ ባለቤት ሁሉ በማገዝ ለውጤት አብቁ የሚል መልዕክቷን በማስተላለፍ አስተያየቷን አሳርጋለች ተመራቂዋ ሳራ።

የ72 ዓመታት ዕድሜ ባለፀጋ የሆነው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዕለተ ቅዳሜ ሐምሌ 9/2014 ዓ.ም ካስመረቃቸው 5 ሺህ 58 ተማሪዎች መካከል የሴት ተማሪዎች ቁጥር ቀላል ባለመሆኑ ይበረታታል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ላይ ካሉት ከ40 ሺህ በላይ ተማሪዎች እንዲሁም ከዚህ ቁጥር ውስጥ 40 በመቶ ከሆኑት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች መካከል 33 በመቶው ሴቶች መሆናቸውም ሴቶች በከፍተኛው ትምህርት መስክ በዚህ ዘመን እምርታ እያሳዩ መምጣታቸው አመላካች ነው።


ተመራቂ እመቤት ረጋሳ


ተመራቂ ሳራ ወልደአማኑኤል



ተመራቂ ትግስት ፍቃዱ

ፎቶ፡- በሰላማዊት ውቤ

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

**በዛሬው ዓምዳችን በ1960 የታተሙት ጋዜጦች ለመቃኘት ሞክረናል ፤በክረምቱ ወቅት የተከሰቱ የሚያሳዝኑ ሁኔታዎች የተካተቱበት ነው፡፡ የሚያሳዝኑ ዜናዎች ቢሆኑም ፈገግ የሚያሰኝ ዜናም አካተናል፡፡**

### አምስት አንበሶች ሁለት ሰው ገደሉ

ነቀምቴ፤-(ኢ-ዜ-አ-) በወለጋ ክፍለ ሀገር በሆሮ ጉድሩ አውራጃ በአመራ ቀበሌ ውስጥ ፭ የአንበሳ መንጋዎች ሁለት ሰዎችና አንድ በሬ ገድለው አንድ ሌላ ሰው ደግሞ ማቁሰላቸው ተገለጠ፡፡

እነኚሁ የአንበሳ መንጋዎች በዚሁ አካባቢ ካለው በረሃ ውስጥ በመውጣት የአቶ ታዬ ቶሌራን አንድ በሬ ይዘው ከበሉ በኋላ ለርዳታ የደረሱትን የበሬውን ባለቤትና አንድ ሌላ ሰው ነክሰው መግደላቸው ታውቋል፡፡

ከዚህም በቀር የቀበሌው የሕዝብ ደህንነት ጥበቃ ጓድ አባሎች ከሥፍራው ደርሰው ርዳታ ለማድረግ በመጣር ላይ እንዳሉ፤ አንደኛው አባል በአንበሶቹ ከተነከሰ በኋላ ይዞት የነበረውም ጠብመንጃ አንደኛው አንበሳ አስጥሎት በጥርሱ ንክሻ በመሸሽ ላይ እንዳለ በአንድ ሌላ ሰው በተተኰሰ ጥይት ተገድሏል፡፡

የቀሩት አራቱ አንበሶች ግን ሸሽተው ወደ ጫካ መግባታቸውን የወረዳው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አስታውቋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፤በነቀምቴ አውራጃ በዋማ ሀገሎ ወረዳ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙት አርሶ አደሮች ፤ፀረ ሰብል የሆኑትን ፪፻፷ አውሬዎች መግደላቸውን ጽሕፈት ቤቱ ጨምሮ አስታውቋል፡፡

**(ሐምሌ 9 ቀን 1969 ዓ.ም የወጣው አዲስ ዘመን)**

### በደሴ የመሬት መንቀጥቀጥ 2 ሰዎች ሲሞቱ 3 ቆሰሉ

ደሴ (ኢ-ዜ-አ-)፡- በወሎ ክፍለ ሀገር በደሴ ከተማና አንዳንድ አውራጃዎች ሐምሌ ፩ ቀን ፷፱ ዓ/ም/ ከጧቱ ፫ ሰዓት ከ፳ ደቂቃ ላይ ደርሶ በነበረው የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ሁለት ሰዎች መሞታቸውን ፫ ሰዎች ደግሞ ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው መሆኑ ተገለጠ፡፡

የደሴ ዙሪያ ወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ስለዚሁ በሰጠው ዜና የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ አልፎ አልፎ ጉዳት ማድረሱን ገልጦ፤ከደሴ ፴ ኪሎ ሜትር ያህል ወደ ገጠር ገባ ብሎ ጦሳ ፈላና በተባለው ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ አንሻ ሙሄና ፋጤ ሙሄ የተባሉ ሁለት ልጃገረዶች እንጨት ለቀማ ሥራ ላይ እንደተሠማሩ በመሬቱ ንዝረት ናዳ ስለተጫናቸው ወዲያውኑ ሞተዋል፡፡ ሌሎች ሦስት ሰዎች ደግሞ ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸው በሕክምና ላይ እንደሚገኙ ተረጋግጧል፡፡

እንዲሁም በቃሉ አውራጃ በፋርጡማ ወረዳ ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ የመሬት መንቀጥቀጥ መድረሱንና በሕይወት ላይ ጉዳት አለማድረሱን የወረዳው አስተዳደር አስታውቋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በደሴ ዙሪያ ወረዳ በሐራ ወደሎ ቀበሌ ባለፈው ሐሙስ በጣለው ኃይለኛ ዝናብ ወቅት በወደቀው መብረቅ እሸቱ የሱፍ የተባለው ሰው ከሁለት በሬችና አንዲት ላም ጋር በዛፍ ሥር እንደተጠለሉ ተመትተው መሞታቸውን የወረዳው የገበሬ ማኅበር የልማት ተጠሪ አረጋግጠዋል፡፡

**(ሐምሌ 3 ቀን 1969 ዓ.ም የወጣው አዲስ ዘመን)**

### ባላገሮችን ያታለሉ ተፈረደባቸው

‹‹ከሀብታሞች ዘንድ ወስደን ገንዘብ እናሰጣለን ››በማለት ከገጠር የሚመጡትን ገበሬዎች ከመንገድ እየጠበቁ አታለው ገንዘብ የወሰዱት ሁለት አታላዮች የ፲፰ ዓመት እሥራት ተፈረደባቸው፡፡

ከአሩሲ ጠቅላይ ግዛት ከአርባ ጉጉ አውራጃ የመጡት አቶ ኢንካ አብዲን ‹‹ ሀብታሞች ለድሃ ገንዘብ ይሰጣሉ›› በማለት ፴ ብርና አንድ ጋቢ አጭበርብሮ የወሰደው ታደሰ ቢነግዴ የ፲ ዓመት እሥራት ትናንት ተፈረደበት፡፡ ከሸዋ ጠቅላይ ግዛት ከሜታ ሮቢ የመጡት አቶ ጐንፋ ሙለታን ‹‹ትልልቅ አዛውንት ገንዘባቸውን በነፃ ለሕዝብ ስለሚያድሉ በኪስዎ ያለውን ገንዘብ ከእኔ ዘንድ አስቀምጠው ብዙ ገንዘብ ተቀብለው ሲመጡ ይወስዳሉ ›› በማለት ፩፻ ብር የወሰደባቸው አሰፋ መንገሻ በ፰ ዓመት እሥራት እንዲቀጣ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትናንት በየነበት ፡፡

ሁለቱም አታላዮች ወይም እንደፖሊሶቹ አጠራር ‹‹እነ ቁጭበሉ ›› በአዲስ አበባ ከተማ አንዳንድ ባላገሮች በማታለል ‹‹ለአርበኞች ፤ለአገለገሉ ፤ለሸመገሉና ምንም ለሌላቸው ሰዎች ገንዘብ በነፃ ይሰጣል፡፡ የያዛችሁትን ሁሉ ከኛ ዘንድ አስቀምጣችሁ ስትመለሱ ትወስዳላችሁ ›› በማለት ይዘው እየጠፉ የሚያታልሉ መሆናቸው ተመስክሮባቸዋል፡፡

ወንጀለኞቹ ደጎና ልብስ እየለበሱ ታማኞችና ሽማግሌዎች በመምሰል ባላገሮችን ‹‹ገንዘብ በነፃ ለመቀበል በምትሄዱበት ጊዜ ተፈትሻችሁ ገንዘብ ከኪሳችሁ የተገኘ እንደሆነ ትወረሳላችሁ ፤ደጎና ልብስ የለበሳችሁ እንደሆነ ትገፈፋላችሁ በማለት›› የሚያታልሉ መሆናቸው በምስክር ተረጋግጦባቸዋል፡፡

**( ሰኔ 15 ቀን 1964 ዓ.ም የወጣው አዲስ ዘመን)**

### ለደስታ የተተኮሰ ጥይት ፩ እድምተኛ ገድሎ ሌላ አቆሰለ

<u>**አዲስ አበባ (ኢ-ዜ-አ-)፡-**</u> በሠርግ በዓል ላይ ለደስታ መግለጫ የተተኮሰው ፴ ጥይት ከዕድምተኞቹ መካከል አንድ ሰው ወዲያውኑ ሲገድል ሌላ አንድ ሰው በጽኑ ያቆሰለ መሆኑን የሸዋ ፖሊስ ማስታወቂያ ክፍል ትናንት ገለጠ።

የቈሰለው ሰው ናዝሬት ኃይለማርያም ማሞ ሆስፒታል በመታከም ላይ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል ።

አደጋው የደረሰው በየረርና ከረዩ አውራጃ በአዳማ ወረዳ ገዳምሶ ከተባለው ቀበሌ ሰኔ ፲፩ ቀን ፷፬ ዓ/ም ከምሽቱ ፩ ሰዓት ላይ ቱጂ ያኢ የተባለው ሰው ጋብቻ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ሙሽራዎቹ ለደስታ መግለጫ ጥይት ሲተኩሱ መሆኑ ተገልጧል።

ስለ አደጋው ሁናቴ የሸዋ ፖሊስ ማስታወቂያ ክፍል በዝርዝር ሲያስረዳ የሙሽራው ዕድምተኞች ከሙሽራዋ ቤት ሲመለሱ ለደስታ መግለጫ ከ፴ ጥይት በላይ በማከታተል በመተኰስ ከዕድምተኞቹ መካከል አንዱ ማሞ ጉርሙ የተባለው በጥይት ተመትቶ ወዲውኑ ሲሞት ፤ባልቻ ኦዳ በጽኑ ቆስሎ በሆስፒታል በመታከም ላይ ይገኛል ካለ በኋላ፤ ሟችና ቁስለኛው በማንኛው ጥይት እንደተመቱ ባለመታወቁ ምርመራውን አስቸጋሪ ያደረገው መሆኑን ጠቅሶ፤ይህ ዓይነቱ አደጋ በገጠር ሥፍራዎች አልፎ አልፎ የሚደርስ በመሆኑ ፤የጋብቻ በዓላቸውን የሚያከብሩ ሁሉ ይህንን ዓይነት ከንቱ ልማድ እንዲተዉና ደስታቸውን ወደ ሀዘን ከመለወጥ እንዲታገዱ አሳስቧል ።

**(ሰኔ 22 ቀን 1964 ዓም የወጣው አዲስ ዘመን)**

# ዓለም አቀፍ



## ዜሌንስኪ ከሀገር ክህደት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ባለሥልጣናትን አባረሩ

ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ዜሌንስኪ ከሀገር ክህደት ጋር የተያያዙ ጥሰቶችን በመጥቀስ የሀገሪቱን የደኅንነት መሥሪያ ቤት (ኤስቢዩ) ኃላፊ እና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግን ከኃላፊነት አነሱ።

በሩሲያ ቁጥጥር ስር በሚገኙ አካባቢዎች ከ60 የሚበልጡ የደኅንነት መሥሪያ ቤቱ የቀድሞ ባልደረቦች ከዩክሬን በተቃራኒ ከሞስኮ ጎን ተሰልፈዋል ብለዋል ፕሬዚዳንቱ። በሕግ አስከባሪ አካላት ላይ ከጠላት ጋር በመወገን እና ከሀገር ክህደት ጋር በተያያዘ 651 ክሶች ተመስርተዋል ብለዋል- ፕሬዚዳንቱ።

ዕሁድ አመሻሽ ላይ ዜሌንስኪ በቪዲዮ በሰጡት መግለጫ "እንዲህ ዓይነቱ የሀገርን ብሔራዊ ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ወንጀሎች… [የሁለቱ ድርጅቶች] ኃላፊዎቹ ላይ በጣም አሳሳቢ ጥያቄዎችን ያስከትላሉ።"ፕሬዚዳንቱ አክለውም "እነዚህ ጥያቄዎች በሙሉ ትክክለኛ ምላሽ ያሻቸዋል" ብለዋል።

የዩክሬን ደኅንነት ተቋም (ኤስቢዩ) ኃላፊዋ ኢቫን ባካኖቭ ከዜሌንስኪ ጋር ከልጅነት ጀምረው ጓደኛሞች ነበሩ ። ኃላፊዋ ከሥራቸው እንዲሰናበቱ የተደረገው እአአ በ2014 ሩሲያ በኃይል በተቆጣጠረቻት ክራይሚያ የቢሮው ኃላፊ የሆኑት ግለሰብ መታሰራቸውን ተከትሎ ነው። በዚህም አሌህ ኩሊንች በሀገር ክህደት ተጠርጥረው ነው በቁጥጥር ስር የዋሉት።

በተያያዘ ዜና ዩክሬን በፈጠረችው ወታደራዊ ጫና በርካታ ቁጥር ያላቸው የሩሲያ የጦር መርከቦች ከክራይሚያ ወደ ምሥራቅ ኖቮሮሲስክ ወደብ ተንቀሳቅሰዋል። ውጤቱ የተገኘው ኪዬቭ ከምዕራባውያን አጋሮቿ ተጨማሪ የረዥም ርቀት ተምዘግዛጊ የሚሳኤሎችን ስለተቀበለች ነው ተብሏል።

አሁን የሩሲያ የፀጥታ ምክር ቤት ኃላፊ በመሆን በማገልገል ላይ የሚገኙት የቀድሞው የሩሲያ ፕሬዚዳንት ዲሚትሪ ሜድቬዴቭ ዩክሬን ክራይሚያን ልትወጋ ከወሰነች "የዓለም ፍጻሜ ይሆንባታል" ሲሉ ማስጠንቀቃቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።


## ጋና ከኢቦላ ጋር ተመሳሳይ በሆነው ቫይረስ ሰዎች መሞታቸውን ይፋ አደረገች

ጋና በፍጥነት እና በቀላሉ ተላላፊ በሆነው ገዳይ ቫይረስ ሁለት ሰዎች መሞታቸውን ይፋ አደረገች። ማርበርግ የተባለው ይህ ቫይረስ ኢቦላን ከሚያመጣው ቫይረስ ጋር ተቀራራቢ ነው።

ሁለቱም ታካሚዎች በደቡባዊ አሻንቲ ግዛት ሕክምና ሲሰጣቸው ቆይቶ ሕይወታቸው አልፏል ተብሏል። በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ የተወሰደው የታማሚዎቹ ናሙና በዚህ ገዳይ ቫይረስ መያዛቸውን ያሳየ ሲሆን፤ ሴኔጋል ያለ ቤተ ሙከራም ይህንኑ አረጋግጧል። የአገሪቱ የጤና ባለሥልጣናት በቫይረሱ ተይዘው ሕይወታቸው ካለፉት ሰዎች ጋር ንክኪ ነበራቸው ተብለው የተጠረጠሩ 98 ሰዎች በለይቶ ማቆያ ውስጥ ይገኛሉ ብለዋል።

ማርበርግ ቫይረስ የሚያስከትለውን ሕመም የሚፈውስ መድኃኒት አልተገኘም። ብዙ ውሃ መጠጣት እና የሚታዩ ምልክቶችን ማከም የታካሚውን የመዳን ዕድል እንደሚያሻሽለው የሕክምና ባለሙያዎች ይናገራሉ። ቫይረሱ ወደ ሰዎች የሚተላለፈው ከሌሊት ወፎች ነው። በሰዎች መካከል ደግሞ ከሰውነት ከሚወጣ ፈሳሽ ጋር በሚኖር ንክኪ አማካኝነት በቀላሉ ይተላለፋል።

በዚህ ገዳይ በሆነው ቫይረስ የተያዙ ሰዎች ከባድ የራስ ምታት፣ ትኩሳት፣ የጡንቻ ሕመም፣ ደም ማስመለስ እና የደም መፍሰስን ምልክት ይታይባቸዋል። ሰዎች የሌሊት ወፎች ሊገኙባቸው ከሚችሉ ዋሻዎች እንዲርቁ እና ሥጋ ሲመገቡ በደንብ እንዲያበስሉ ባለሥልጣናት እያስጠነቀቁ ነው። እንደ የዓለም ጤና ድርጅት ከሆነ ይህ ቫይረስ አፍሪካ ውስጥ ቀደም ሲል በአንጎላ፣ በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ፣ በኬንያ፣ በደቡብ አፍሪካ እና በኡጋንዳ በተለያየ ደረጃ ተከስቶ ነበር።



የመጀመሪያው የማርበርግ ወረርሽኝ እአአ በ1967 ጀርመን ውስጥ የተከሰተ ሲሆን ሰባት ሰዎችም ሕይወታቸውን አጥተዋል። እአአ በ2005 በቫይረሱ ምክንያት ከ200 በላይ ሰዎች አንጎላ ውስጥ ሕይወታቸው አልፏል። ይህም በዓለም አቀፍ የጤና ድርጅት እጅግ የከፋው ነው ተብሎ ተመዝግቧል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

ማክሰኞ አዲስ ዘመን ስፖርት


ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ጎይተቶም ገብረሥላሴ በሴቶች ማራቶን ጣፋጭ ድል አስመዘገበች

**ቦጋለ አበበ**

ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ውድድሮች አውራ ማራቶን በታላቁ የኦሊምፒክ መድረክ በሁለቱም ጾታ ድል በማድረግ ከአፍሪካ ቀዳሚ ናት። ታላቁ አትሌት አበበ ቢቂላ የወንዶች ማራቶን የአፍሪካውያን የድል ፋና ወጊ ነው። በሴቶች ደግሞ ታሪካዊቷ ፋጡማ ሮባ ፈርቀዳጅ ናት። እንደ አጠቃላይ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በኦሊምፒክ የማራቶን ውድድሮች በሁለቱም ጾታ ደጋግመው ወርቅ ያጠለቁበት ታሪክ አላቸው። ወደ ዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ስንመጣ ግን የኢትዮጵያውያን አትሌቶች የማራቶን ድል በተለይም በሴቶች ከኦሊምፒክ አኳያ ደብዛዛ ነው። በእርግጥ የወንድ አትሌቶችም ውጤት ያለፈውና የዘንድሮው ቻምፒዮና ድሎች ታሪክ መቀየር ቻሉ እንጂ ተመሳሳይ ነበሩ።

በርካታ ኢትዮጵያውያን ሴት አትሌቶች በየዘመኑ በማራቶን የግል ውድድሮች ስኬታማ መሆን ቢችሉም በዓለም ቻምፒዮና መድረክ ግን ነጥረው መውጣት እንዳልቻሉ ያለፉት ውድድሮች ውጤታቸው ማሳያ ነው። በዚህ መድረክ የኢትዮጵያ ብቸኛውና የመጀመሪያው የወርቅ ሜዳሊያ እኤአ በ2015 የቤጂንግ የዓለም ቻምፒዮና በማሬ ዲባባ የተመዘገበው ነው። ከዚህ ውጪ ሊጠቀስ የሚችለው ብቸኛ ሜዳሊያ እኤአ በ2009 የበርሊን ቻምፒዮና አሰለፈች መርጊያ ያስመዘገበችው ነሐስ ነው። እነዚህ ሁለት ሜዳሊያዎች ብቻ ኢትዮጵያን ከዓለም ስድስተኛ ደረጃ ላይ አስቀምጠዋት ቆይተዋል።




በአንጻሩ ኬንያ በ4ወርቅ፣ 4ብርና 1 ነሐስ ቀዳሚውን ደረጃ ይዛለች። ጃፓን በ2ወርቅ፣ 5ብርና 4 ነሐስ ተከታዩን ደረጃ ስትይዝ፣ ፖርቱጋል 2ወርቅና 2ብር በታሪኳ አስመዝግባ ትከተላለች። ሮማኒያ 1ወርቅ፣ 1ብርና 3 ነሐስ ያላት አገር ስትሆን ቻይና በ1ወርቅና 1 ብር ከኢትዮጵያ በላይ የሚቀመጡ አገራት ነበሩ። ዛሬ በኦሪገን እየተካሄደ በሚገኘው የዓለም ቻምፒዮና ይህን ታሪክ የቀየረ ድል በወጣቷ ድንቅ ኢትዮጵያዊት አትሌት ጎይተቶም ገብረሥላሴ ተመዝግቧል። ከመጀመሪያ አንስቶ እስከ ፍፃሜው ድረስ በኢትዮጵያውያንና ኬንያውያን አትሌቶች የታክቲክ ጦርነት ልብ አንጠልጣይ በሆነ ፉክክር የታጀበው የሴቶች ማራቶን የወርቅ ሜዳሊያ የማታ ማታ ማረፊያውን ኢትዮጵያ አድርጓል።

አትሌት ጎይተቶም በውድድሩ ታሪክ ለኢትዮጵያ ሁለተኛውን የርቀቱ የወርቅ ሜዳሊያ ስታዝመዘግብ በእንግሊዛዊቷ አትሌት ፓውላ ራድክሊፍ ተይዞ ለዓመታት የቆየው የቻምፒዮናው ክብረወሰን 2፡18፡11 በሆነ ሰዓት ተሰብሯል።ትናንትም በተመሳሳይ በወንዶች ማራቶን አትሌት ታምራት ቶላ ለኢትዮጵያ ወርቅ ሲያስመዘግብ የቻምፒዮናውን ክብረወሰን በማሻሻል ጭምር መሆኑ ለኢትዮጵያውያን ድሉ እጥፍ ድርብ ሆኗል።በአንድ ቻምፒዮና ኢትዮጵያ በሁለቱም ፆታ የማራቶን ወርቆችን ስታስመዘግብም በታሪክ የመጀመሪያ ሆኗል።ጎይተቶም ምንም እንኳን በውድድሩ መሃል ህመም ተሰምቷት የነበረ ቢሆንም በታላቅ ፅናት እስከ መጨረሻ ለመጓዝ አላመነታችም።ይህም እኤአ በ2007 የኦሳካ የዓለም ቻምፒዮና ጥሩነሽ ዲባባ ሆዷን ይዛ ለወርቅ እንደበቃችው ሁሉ ጎይተቶምም ተመሳሳይ ታሪክ ደግማለች።

ውድድሩ 8ኪሎ ሜትር እስኪቀረው ድረስ የነሐስ ሜዳሊያ ለማጥለቅ የተፋለመችው ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት አባብል የሻነህ ስኬታማ ሊባል የሚችል የቡድን ሥራ ብትሠራም አቋርጣ ለመውጣት ተገዳለች።በዚህም በታክቲክ ጦርነቱ ከአርባ ኪሎ ሜትር በኋላ በጎይተቶም የበላይነት የተወሰደባት ኬንያዊቷ ጁዲዝ ኮሪር 2፡18፡20 በመግባት የብር ሜዳሊያውን ወስዳለች።በፅናትና ተስፋ አለመቁረጥ ከአባብል እጅግ ርቃ የነበረችው ትውልደ ኬንያዊት የእሥራዔል አትሌት በመጨረሻም በ2፡20፡18 የነሐስ ሜዳሊያ አሸናፊ ለመሆን በቅታለች።

ECC
የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)

ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

# የግብርና ምርቶችን «ብራንድ» በማድረግ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ

**በአስምነህ ቸርነት**

«ብራንድ» አንድን ምርት ከሌላኛው ተመሳሳይ ምርት መለየት የሚያስችልና ምርቱን በሚጠቀም ደንበኛ ወይም ሸማች ፍላጎት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ማሳደር መቻል ነው። ብራንድ የአንድን ምርት ጥራት አስጠብቆ ለማምረት ቃል መግባት ነው። በኅብረት ሥራ ማኅበራት አማካኝነት ለገበያ ከሚቀርቡ የግብርና ምርቶች መካከል በቀዳሚነት ብራንድ ለማድረግ በኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ተመርጠው ሰሞኑን ብራንድ የተደረጉ ምርቶች የአርባ ምንጭ ሙዝ፣ የአዊ ድንችና የጨንቻ አፕል ናቸው።

ሙዝ በኢትዮጵያ በአብዛኛው ቦታ የሚመረት ቢሆንም በዋናነት የሚመረተው ግን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነው። በደቡብ ክልል በጋሞ ዞን የሚገኘው አርባ ምንጭ በሙዝ ምርት የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል።

በአርባ ምንጭ የሙዝ ምርታማነት ከመስኖ ጋር ተያይዞ በየጊዜው እያደገ መጥቷል። በዞኑ የሙዝ ምርት አነስተኛ ማሳ ላይ በሚያመርቱ በ140ሺ 355 አርሶ አደሮች አማካኝነት በ 37ሺ 841 ሄክታር ማሳ ላይ እየለማ ይገኛል። በአርባ ምንጭ በሄክታር በአማካይ ከ144 እስከ 219 ኩንታል ሙዝ ምርት ይመረታል። አካባቢው ከ30 ዓመታት በላይ ኦርጋኒክ ሙዝ ያመረተ ለም መሬት ያለው ነው። አብዛኛው አርሶ አደሮች በተፈጥሮ የሚገኙ እንደ ፍግ ያሉ ማዳበሪያዎችን ይጠቀማሉ። በአሁኑ ጊዜ የዞኑ ግብርና ምርምር ማዕከል በሽታ የሚቋቋሙና የበለጠ ምርት የሚሰጡ አዳዲስ ዝርያዎች የማበልጸግ ሥራ እየሠራ ሲሆን በሄክታር 428 ኩንታል ምርት ሊሰጥ እንደሚችል በሙከራ ተረጋግጧል። የሙዝ ምርት በአርባ ምንጭ ከጥቅምት እስከ ጥር ባሉት ወራት ከፍተኛ ምርት የሚገኝበት ወቅት ቢሆንም ምርቱ ከዘጠኝ እስከ 10 ወራት ይመረታል።

የአርባ ምንጭ ሙዝ በኢትዮጵያ በስፋት ዕውቅና ካላቸው የሙዝ ዝርያዎች ቀዳሚው ሲሆን በኦርጋኒክነቱ፣ በተለየ ጣዕሙና ጥራቱ እንዲሁም ባለው ረጅም የቆይታ ግዜ ይወደዳል። በሀገራችን ድንች በአማራ ክልል በስፋት የሚመረት ሲሆን ምርቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደመጣ መረጃዎች ያሳያሉ። በአማራ ክልል በአዊ ዞን፣ በሰሜንና ደቡብ ጎንደርና በምስራቅና ምዕራብ ጎጃም በስፋት ይመረታል።




በአዊ ዞን በአነስተኛ ማሳ ላይ የተሰማሩ 69ሺ 948 አርሶ አደሮች በ10ሺ 332 ሄክታር የእርሻ መሬት ላይ የድንች ምርት እያመረቱ ይገኛሉ። የአዊ ዞን አግሮ ኢኮሎጂ ድንችን ለማምረት እጅግ ተስማሚ ነው። የድንች ምርት በአዊ ዞን በዓመት ሦስት ጊዜ የሚደርስ ሲሆን በመስከረም አጋማሽ፣ በየካቲት መጀመሪያና በግንቦት መጀመሪያ ላይ ምርት ተሰብስቦ ለገበያ የሚቀርቡበት ወቅት ነው። የክልሉ ግብርና መረጃ እንደሚያሳየው በምርምር 400 ኩንታል እና በአርሶ አደር መሬት ደግሞ ከ300 ኩንታል በላይ በሄክታር ይመረታል። የአዊ ድንች የተጠቀጠቀ፣ ጥሩ ቅርጽና ልስላሴ ያለው ሲሆን በተለያየ የምግብ አይነት ተቀቅሎ፣ ተጋግሮና ተጠብሶ ሊበላ የሚችል ኃይል ሰጭና ሌሎች የምግብ ንጥረ ነገር ይዘቶች የያዘ ነው።




የአፕል ፍራፍሬ በተለያዩ የሀገራችን ተራራማና ቀዝቃዛ ቦታዎች ይበቅላል። በደቡብ ክልል እንደ ጋሞ፣ ጉራጌ፣ ጌዶ፣ ሲዳማ ያሉት ዞኖች የአፕል አምራች አካባቢዎች ናቸው። በጋሞ ዞን በጨንቻ ደጋማ ቦታ አፕል በስፋት እየተመረተ ይገኛል። በጨንቻ ወረዳ በአነስተኛ ማሳ ላይ የአፕል ፍራፍሬ ምርት የሚያመርቱ 242ሺ 906 አርሶ አደሮች በሰባት ሺ 773 ሄክታር እርሻ መሬት ላይ ምርቱን እያለሙ ይገኛሉ። ቀደም ሲል በጋሞ ዞን በጨንቻ ወረዳ ብቻ ይመረት የነበረው አፕል ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዞኑ ሌሎች ሰባት ወረዳዎች እየተስፋፋ መጥቷል። በመሆኑም የአፕል ምርት በመጠን ሽፋንና በተሳታፊ አርሶ አደር ብዛት ከዓመት ወደ ዓመት እያደገ ነው። በጋሞ ዞን ከፍተኛ የአፕል ምርት ከየካቲት እስከ ሚያዚያ ባሉት ወራት ይመረታል። በዞኑ የአፕል ምርታማነትን ለማሳደግ የተፈጥሮ ማዳበሪያ የመጠቀምና ዝርያዎችን የማሻሻል ሥራ እየተሠራ ነው። የጨንቻ አፕል ባለው ልዩ ጣዕም፣ አነስተኛ የአሲድ መጠን፣ በውስጡ በያዘው የፈሳሽ ይዘቱ፣ ጥቅጥቅ ያለ መሆኑና ሲበላ ለጥርስ ምቾት ያለው መሆኑ የተለየ ያደርገዋል።




በኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን አነሳሽነት በኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት የሚመረቱ የአርባ ምንጭ ሙዝ፣ የአዊ ድንች እና የጨንቻ አፕል ምርቶች አዳዲስ የብራንድ መለያዎች ሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም በይፋ የማስተዋወቅ ሥነ ሥርዓት ተከናውኗል። ብራንድ የተደረጉትን የግብርና ምርቶች በሀገር አቀፍ ገበያ በስፋት ተደራሽ የመሆን ትልቅ ዕምቅ አቅም ያላቸው ቢሆኑም በአሁኑ ግዜ በደካማ የግብይት ትስስር፣ በገበያ መሠረተ ልማት እጦት እና በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ጥቂት የሚባሉ ነጋዴዎችና ደላሎች እንዳሻቸው የዋጋ ተመን በማውጣት ገበያውን በሚቆጣጠሩበት የተዛባ የግብይት ስርዓት በመገደባቸው አምራቹም ሆነ ሸማቹ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል። በመሆኑም የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ እጅና ጓንት ሆነው መሥራት ይኖርባቸዋል።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et